የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፶፪
አዲስ አበባ ግንቦት ፲፪ ቀን ፲፱፻፺፩

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

5th Year No. 52
ADDIS ABABA - 20th May, 1999

ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፵፱/፲፱፻፺፩ ዓ.ም.
የኤሌክትሪክ ሥራዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት
ደንብ ...................................................... ገጽ ፩ሺ፳፯

CONTENTS

Council of Ministers Regulations No. 49/1999
Electricity Operations Council of Ministers Regulations ........................................ Page 1027

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፵፱/፲፱፻፺፩

## ስለኤሌክትሪክ ሥራዎች የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና በኤሌክትሪክ አዋጅ ቁጥር ፹፮/፲፱፻፹፱ አንቀጽ ፳፰ (፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

፩· አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኤሌክትሪክ ሥራዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፵፱/፲፱፻፺፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡

፩· "አዋጅ" ማለት የኤሌክትሪክ አዋጅ ቁጥር ፹፮/፲፱፻፹፱ ሲሆን በአዋጁ ለተዘረዘሩት ቃላት የተሰጡት ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ተፈጻሚ ይሆናሉ፤

፪· "ኤጀንሲ" ማለት የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኤጀንሲ ነው፤

፫· "የማመንጫ ተቋም" ማለት ኤሌክትሪክ ለማመንጨት የሚያገለግል የቴክኖሎጂ ስብስብ ነው፤

፬· "ከፍተኛ የኃይል ፍላጎት" ማለት በኤሌክትሪክ ተጠቃሚዎች በተወሰነ የጊዜ ክልል ውስጥ የሚከሰት ከፍተኛው የፍጆታ መጠን ነው፤

፭· "ቋሚ የሲስተም ጭነት" ማለት በኃይል አቅርቦት ተቋም ላይ በተከታታይነት የሚታይ የፍጆታ መጠን ነው፤

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS NO. 49/1999
## COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO PROVIDE FOR THE REGULATIONS OF ELECTRICITY OPERATIONS

These Rgulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995 and Article 28 (1) of the Electricity Proclamation No. 86/1997.

### *PART ONE*
### *General*

1. *Short Title*

These Regulations may be cited as the "Electricity Operations Council of Ministers Regulations No. 49/1999."

2. *Definitions*

In these Regulations, unless the context requires otherwise:

1) "Proclamation" means the Electricity Proclamation No. 86/1997, and definitions provided therein shall also apply to these Regulations;
2) "Agency" means the Ethiopian Electricity Agency;
3) "Generation facility" means a set of technology used to produce electricity;
4) "Peak demand" means the highest level demand for electricity achieved by electricity users within a defined period of time;
5) "System based load" means a defined amount of demand for electricity continuously available in the supply system;

ያንዱ ዋጋ 6·00
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፮· "ማርጅናል የማመንጫ አቅም ዋጋ" ማለት በኪሎዋት የሚተመን አንድ ተጨማሪ ኃይል ለማመንጨት የሚያስ ፈልግ ወጪ ነው፡

፯· "ማርጅናል የኢነርጂ ዋጋ" ማለት በኪሎዋት ሰዓት የሚተመን አንድ ተጨማሪ ኢነርጂ ለማምረት የሚያስ ፈልግ ወጪ ነው፡

፰· "የሲስተም ማመንጫ ዋጋ" ማለት በኃይል አቅርቦት ተቋም ውስጥ የተለያየ የማመንጫ ዋጋ ሊኖራቸው በሚችል የኤሌክትሪክ ማመንጫ ቴክኖሎጂዎች የሚመ ነጨውን ኢነርጂ የሚወክል አንድ የኢነርጂ ዋጋ ነው።

፱· "የሲስተም ማርጅናል ማስተላለፊያ አቅም ዋጋ" ማለት በኪሎዋት የሚለካ አንድ ተጨማሪ የኤሌክትሪክ ኃይል ለማስተላለፍና ትራንስፎርም ለማድረግ የሚያስፈልግ ወጪ ነው፡

፲· "የሲስተም ማርጅናል የማከፋፈያ አቅም ዋጋ" ማለት በኪሎዋት የሚለካ አንድ ተጨማሪ የኤሌክትሪክ ኃይል ለማከፋፈልና ትራንስፎርም ለማድረግ የሚያስፈልግ ወጪ ነው፡

፲፩· "ከፍተኛ ቮልቴጅ" ማለት ከ፷ሺ ቮልት በላይ የሆነ የቮልቴጅ መጠን ነው፡

፲፪· "መካከለኛ ቮልቴጅ" ማለት ከ፩ሺ በላይ እስከ ፷ሺ ቮልት የሆነ የቮልቴጅ መጠን ነው፡

፲፫· "ዝቅተኛ ቮልቴጅ" ማለት እስከ ፩ሺ ቮልት የሆነ የቮልቴጅ መጠን ነው፡

፲፬· "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

## ክፍል ሁለት
## ስለኤሌክትሪክ ሥራ ፈቃዶች
### ምዕራፍ አንድ
### ስለፈቃድ ማመልከቻዎች

፫· ጠቅላላ

፩· የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት፡ ለማስተላለፍ፡ ለማከፋፈልና ለመሸጥ፡ እንዲሁም ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ወይም ወደ ውጭ ለመላክ የሚያስችል ፈቃድ ለማግኘት ለኤጀንሲው የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡

ሀ) የአመልካቹን ማንነትና አድራሻ፡

ለ) የፕሮጀክቱን የፊዚቢሊቲ ጥናት፡

ሐ) የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት፡

መ) የአመልካቹን የፋይናንስ ሁኔታ፡ የቴክኒክ ብቃትና ልምድ የሚያሳዩ ሠነዶች፡

ሠ) የግንባታና ኢንስታሌሽን ዲዛይን፡ እና

ረ) ኤጀንሲው ያስፈልጋል ብሎ በመመሪያ የሚወስ ናቸው ሌሎች መረጃዎች።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ለ) የተመለከተው የፊዚ ቢሊቲ ጥናት የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡

ሀ) የማህበራዊና ኢኮኖሚ ተፅዕኖ ጥናት፡

ለ) የፕሮጀክቱን ወጪና ገቢ ግምት፡

ሐ) ፕሮጀክቱ የሚቆይበትን ጊዜ፡

መ) የግንባታና የኢንስታሌሽን ፕሮግራምና አገል ግሎት መስጠት የሚጀመርበትን ቀን።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ሐ) የተመለከተው የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡



6) "marginal generation capacity cost" means the cost associated with producing one additional unit of power expressed in kilo watt;

7) "marginal energy cost" means the cost associated with producing one additional unit of energy expressed in kilo watt hour;

8) "system generation price" means a single price of power or energy prevailing in the supply system which in effect consists of different generation technologies bearing different unit cost of generation;

9) "system marginal transmission capacity cost" means the cost associated with transporting and transforming one additional unit of power expressed in kilo watt;

10) "system marginal distribution capacity cost" means the cost associated with distributing and transforming one additional unit of power expressed in kilo watt;

11) "high voltage" means a voltage level above 60,000 volt;

12) "medium voltage" means a voltage level above 1000 but less than 60,000 volt;

13) "low voltage" means a voltage level up to 1000 volt;

14) "person" means a natural or a juridical person.

## *PART TWO*
## *Electricity Operation Licenses*
### *CHAPATER ONE*
### *Applications for License*

3. *General Requirements*

1) Any application for a license of generation, transmission, distribution and sale, as well as application for importation or exportation of electricity shall be addressed to the Agency and shall contain:

(a) identity and address of the applicant;

(b) feasibility study of the project;

(c) environmental impact assessment;

(d) documents showing the applicant's financial situation, technical competence and experience;

(e) construction and installation designs, and

(f) such other information the Agency may determine by directives.

2) The feasibility study referred to in sub-article 1 (b) of this Article shall consist of the following components:

(a) social and economic impacts;

(b) estimated costs and returns of the project;

(c) duration of the project;

(d) construction and installation program and commencement date of operation.

3) The environmental impact assessment referred to in Sub-Article 1 (c) of this Aricle shall consist of the following components:

ሀ) በአካባቢ ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ማናቸውንም ጉዳዮች እና እነዚህኑ ለማቃለል የሚያስችል እንዲሁም አካባቢውን ወደ ቀድሞው ሁኔታ ለመመለስ ወይም ለሌላ ጥቅም ለማዋል የሚያስችል ዕቅድና የሚፈናቀሉ ሰዎችን መልሶ የማቋቋሚያ ፕሮግራም፣

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ (ሀ) የተመለከቱትን ዕቅዶችና ፕሮግራሞች ለመተግበር የሚያስፈልገውን ወጪ ግምት።

፬· የዚህ ደንብ አንቀጽ ፱ እና ፲ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማንኛውም አመልካች ለኤጀንሲው የሚያቀርባቸው መረጃዎች በምስጢር መጠበቅ አለባቸው።

፬· ለኤሌክትሪክ ማመንጨት ፈቃድ ስለሚቀርብ ማመልከቻ

የኤሌክትሪክ ማመንጨት ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማናቸውም ማመልከቻ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ ከተመለከቱት አጠቃላይ ሁኔታዎች በተጨማሪ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፣

፩· የኤሌክትሪክ መገኛውን ምንጭ፣

፪· ኤጀንሲው በሚወስነው ስኬል መሠረት የተዘጋጀ የፕሮጀክቱን ቦታ የሚያሳይ ካርታ፣

፫· የኤሌክትሪክ ፕሮጀክቱ አጠቃላይ የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት አቅም፣

፬· እንደአግባቡ የኤሌክትሪክ ኃይል ግዢ ውል።

፭· ለኤሌክትሪክ ማስተላለፍ ፈቃድ ስለሚቀርብ ማመልከቻ

የኤሌክትሪክ ማስተላለፍ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ ከተመለከቱት አጠቃላይ ሁኔታዎች በተጨማሪ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፣

፩· ዋናና አማራጭ የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ መስመሮች አቋርጠው የሚያልፉባቸውን ሥፍራዎች የሚጠቁም ካርታ፣

፪· የማስተላለፊያ መስመሮች ጠቅላላ ርዝመትና የሚያስተላልፉት ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል ጭነት መጠን፣

፫· የቮልቴጁን ደረጃና ፍሪኩዌንሲ።

፮· ኤሌክትሪክ ለማከፋፈልና ለመሸጥ ፈቃድ ስለሚቀርብ ማመልከቻ

የኤሌክትሪክ ማከፋፈልና መሸጥ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ ከተመለከቱት አጠቃላይ ሁኔታዎች በተጨማሪ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፣

፩· የማከፋፈያ ጣቢያው ኤሌክትሪክ የሚያገኝበትን ምንጭ፣

፪· ከፕሮጀክቱ ተጠቃሚ ይሆናሉ ተብለው የሚገመቱ ደንበኞችን ብዛትና የኤሌክትሪክ ኃይል መሸጫ ዋጋ፣

፫· እንደአግባቡ የኤሌክትሪክ ኃይል ግዥ ውል።

፯· ለኤሌክትሪክ አስመጭነት ወይም ላኪነት ፈቃድ ስለሚቀርብ ማመልከቻ

ኤሌክትሪክ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ወይም ወደ ውጭ ሀገር ለመላክ የሚያስችል ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ ከተመለከቱት አግባብ ካላቸው አጠቃላይ ሁኔታዎች በተጨማሪ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፣

፩· ኤሌክትሪክ ከሚያስመጣበት ወይም ከሚልክበት ሀገር ጉዳዩ ከሚመለከተው ባለሥልጣን ጋር የተደረገ ስምምነት፣

፪· የቮልቴጁንና የፍሪኩዌንሲውን ደረጃ፣

፫· እንደአግባቡ የኤሌክትሪክ ኃይል ግዢ ውል።

(a) all potential damages to the environment along with mitigation,restoration or reclamation plan including resettlement program for displaced residents;

(b) the estimated costs of implementation of the plans and programs referred to in paragraph (a) of this Sub-Article.

4) Without prejudice to the provisions of Articles 9 and 10 of these Regulations, information provided to the Agency by any applicant shall be confidential.

4. *Application for Generation License*

Any application for a generation license shall, in addition to the general requirements stated under Article 3 of these Regulations, contain the following:

1) source of electricity;
2) map of the project site at the scale determined by the Agency;
3) total power capacity of the project;
4) power purchase contract where appropriate.

5. *Application for Transmission License*

Application for transmission license shall, in addition to the general requirements stated under Article 3 of these Regulations, contain the following:

1) preliminary route map of proposed main and alternative transmission lines;
2) total length and maximum load of transmission lines,
3) Standard of voltage and frequency.

6. *Application for Distribution and Sale of Electricity License*

Application for distribution and sale of electricity license shall, in addition to the general requirements stated under Article 3 of these Regulations, contain the following:

1) the source from which the distribution system draws electricity;
2) estimated number of customers to be benefited from the project and proposed price of each unit of power to be sold;
3) power purchase contract where appropriate.

7. *Application for Importation and Exportation License*

Application for importation or exportation license shall, in addition to the relevant general requirements stated under Article 3 of these Regulations, contain the following:

1) an agreement made with concerned authority of a country from which or to which electricity is imported or exported;
2) standard of voltage and frequency;
3) power purchase contract where appropriate.

## ምዕራፍ ሁለት
## ስለማመልከቻ ምዝገባና ማስታወቂያ

፰· ማመልከቻን ስለመመዝገብ

እያንዳንዱ ማመልከቻ በዚህ ደንብ ምዕራፍ አንድ መሠረት በትክክለኛው ፎርም ተሟልቶ ሲቀርብ ኤጀንሲው ለዚሁ ተግባር ባዘጋጀው መዝገብ ላይ እንደአቀራረቡ ቅደም ተከተል ወዲያውኑ ይመዘግበዋል ፤ እያንዳንዱ አመልካችም የምዝገባውን ቀንና ቁጥሩን የሚገልጽ ደረሰኝ ይሰጠዋል ።

፱· ማመልከቻን ስለማስታወቅ

፩· ፈቃድ ለማግኘት የቀረበው ማመልከቻ ማስታወቂያ በሀገሪቱ ውስጥ ሰፊ ስርጭት ባላቸው ጋዜጦች በሁለት ተከታታይ እትሞች እንዲወጣ ኤጀንሲው ማመልከቻው በተመዘገበ በሦስት የሥራ ቀናት ውስጥ ማስታወቂያውን ለሚመለከተው አሳታሚ ይልካል ።

፪· ማስታወቂያው የፈቃዱን ዓይነት ፤ ዓላማና የፈቃዱን ሥፍራ የሚገልጽና የካርታ ቅጅዎች የሚታዩበትን ወይም የሚገዙበትን አድራሻና ጉዳዩ ይመለከተኛል የሚል ማናቸውም ሰው ያለውን ተቃውሞ ወይም አስተያየት የሚያቀርብበትን የኤጀንሲውን አድራሻ የሚገልጽ መሆን አለበት ።

፫· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማስታወቂያው ለሦስት ተከታታይ ቀናት በሬዲዮና በቴሌቪዥን መነገር አለበት ።

፬· አመልካቹ ለማስታወቂያው የሚያስፈልጉትን ወጪዎች በሙሉ ይሸፍናል ።

፲· የካርታዎችን ቅጅዎች በይፋ እንዲታዩ ስለማድረግ

አመልካቹ የፈቃዱን ሥፍራ የሚያሳዩት የካርታ ቅጅዎች በይፋ እንዲታዩ በኤጀንሲው ቢሮና ፈቃዱ በተጠየቀበት አካባቢ ባለ የከተማ መስተዳድር ጽ/ቤት ማስቀመጥ አለበት ።

፲፩· መቃወሚያዎችን ስለማቅረብ

፩· ማንኛውም ጉዳዩ ይመለከተኛል የሚል ሰው ማስታወቂያው በጋዜጣ ለመጨረሻ ጊዜ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ፷ ቀናት ውስጥ በተጠየቀው ፈቃድ ላይ ያለውን ተቃውሞ ወይም አስተያየት ከነምክንያቶቹ በጽሁፍ ለኤጀንሲው ሊያቀርብ ይችላል ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የቀረበ መቃወሚያ ውድቅ ከተደረገ፣ ኤጀንሲው ውሳኔውን ከነምክንያቱ በጽሑፍ ገልጾ ለተቃዋሚው እንዲደርሰው ያደርጋል ።

፲፪· ማመልከቻን ስለማሻሻል

ማመልከቻውን ለማሻሻል የሚፈልግ ማናቸውም አመልካች ማሻሻያውን ለኤጀንሲው በጽሁፍ ማቅረብ አለበት ። የዚህ ምዕራፍ ድንጋጌዎች በቀረበው ማሻሻያ ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ ።

## ምዕራፍ ሦስት
## ፈቃድ ስለመስጠትና ስለመከልከል

፲፫· ፈቃድ ስለመስጠት

፩· በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፩ በተጠቀሰው የ፷ ቀናት ጊዜ ውስጥ በማመልከቻው ላይ ምንም ዓይነት መቃወሚያ ካልቀረበና ኤጀንሲው በአመልካቹ የተጠየቀው ፈቃድ የሚያስከትላቸውን ግዴታዎች ለመወጣት የሚያስችል የፋይናንስ ምንጭ ፤ የቴክኒክ ችሎታና ልምድ አመልካቹ ያለው መሆኑን ሲያምንበት የተወሰነውን ክፍያ በማስከፈል በ፴ ቀናት ውስጥ ፈቃዱን ይሰጠዋል።

## *CHAPTER TWO*
## *Registration And Advertisement of Application*

8. *Registration of Application*

Each application for license, if complete and in the proper form as provided in Chapter One of these Regulations, shall immediately be registered in the register maintained in the office of the Agency for such purpose in the order received, and each applicant shall upon such registration be given a receipt indicating the date and number thereof.

9. *Advertisement of Application*

1) The Agency shall, within three working days after the registration of an application of license, send notice of the application to the concerned publishers for publication on two successive issues of news papers which have wider circulation in the country.

2) The advertisement shall describe the type, purpose and area of license and shall give the address of the offices where copies of maps may be inspected or purchased, and shall specify the address of the Agency to which an objection or comment may be forwarded by any interested person.

3) Without prejudice to the provisions of Sub-Articles (1) and (2) of this Article, the advertisement shall be announced on the Radio and TV for three consecutive days.

4) The applicant shall bear costs necessary for such an advertisement.

10. *Deposition of Copies of Maps for Public Inspection*

The applicant shall deposit copies of the maps of the proposed area of license for public inspection at the office of the Agency and the municipality of proposed area of license.

11. *Lodging of Objections*

1) Within 60 days from the last publication of the advertisement on the newspaper any interested person may file at the office of the Agency a written objection against the proposed license or may forward any comment stating the reasons thereof.

2) If an objection filed by any person pursuant to Sub-Article (1) of this Article is rejected, the Agency shall so notify the person in writing setting the reasons for decision.

12. *Amendment of Application*

If an applicant desires to make any amendment to his application, he shall submit a written application to the Agency. Such application shall also be subject to the provisions of this Chapter.

## *CHAPTER THREE*
## *Issuance and Refusal of License*

13. *Grant of License*

1) If, upon the expiry of the 60 days period specified under Article 11 of these Regulations no objection to the application has been filed at its office, the Agency shall, upon payment by the applicant of the prescribed fees, grant the requested license within 30 days; provided, however, that no license shall be granted unless the Agency is satisfied that the applicant has the necessary financial resource, technical competence and experience to meet the obligations relating to the license requested.

፪· በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፩ መሠረት በማመልከቻው ላይ ተቃውሞ ከቀረበ ፈቃድ የመስጠቱ ሂደት ማመልከቻው በኤጀንሲው ከተመዘገበ ከ፩፻፳ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በተቃውሞው ላይ ውሳኔ እስከሚሰጥበት ድረስ ይዘገያል ። የተሰጠው ውሳኔ ተቃውሞውን ውድቅ የሚያደርግ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካቹ ወዲያውኑ ፈቃድ ይሰጠዋል ።

፫· አመልካቹ አግባብ ባለው የኢንቨስትመንት ሕግ መሠረት ኢንቨስት ለማድረግ የሚፈቀድለት ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ መሠረት ፈቃድ አይሰጠውም ።

፲፬· ፈቃድን ስለመከልከል

፩· ኤጀንሲው የቀረበው ማመልከቻ ወይም ተያይዞ የቀረበው መረጃ ወይም የአመልካቹ የፋይናንስ አቅም፣ የቴክኒክ ችሎታና ልምድ በቂ አይደለም ብሎ ከወሰነ ይህንኑ ከነምክንያቱ ለአመልካቹ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት ።

፪· አመልካቹ የሚደግፉትን መረጃዎች ለማቅረብ እንዲችል ኤጀንሲውን የማማከር ዕድልና የቀረበበትን ተቃውሞ ለመቋቋም ከ፴ ቀናት ያላነሰ ጊዜ ይሰጠዋል ፤ እንዲሁም ማመልከቻውን የማረም ወይም የማሟላት መብት ይኖረዋል።

፫· አመልካቹ የኤጀንሲውን ምክር ካገኘና የተሰጠው ጊዜ ካለፈም በኋላ ኤጀንሲው ማመልከቻው ወይም የቀረበው መረጃ ወይም የአመልካቹ ችሎታ የጠየቀውን ፈቃድ ለመስጠት የማያበቃ መሆኑን ሲያምንበት ይህንኑ ለአመልካቹ በጽሁፍ ያሳውቀዋል ።

፲፭· የፈቃድ ቅጅ ስለመስጠትና ስለመተካት

፩· ባለፈቃዱ የተወሰነውን ክፍያ በመክፈል አንድ ወይም ተጨማሪ የፈቃዱን ቅጂዎች እንዲሰጠው ሊጠይቅ ይችላል ። ኤጀንሲውም ጥያቄው እንደደረሰው የፈቃዱን የተረጋገጠ ቅጂ አዘጋጅቶ መስጠት አለበት ።

፪· ባለፈቃዱ የተወሰነውን ክፍያ ከፍሎ የጠፋበትን ወይም የተበላሸበትን ፈቃድ ምትክ እንዲሰጠው ኤጀንሲውን ሊጠይቅ ይችላል ። ኤጀንሲውም ጥያቄው እንደደረሰው የጠፋውን ወይም የተበላሸውን ፈቃድ ምትክ አዘጋጅቶ መስጠት አለበት ።

፲፮· ፈቃድ ስለማስተላለፍ

ማንኛውም ባለፈቃድ በአዋጁ አንቀጽ ፲፪ ድንጋጌዎች መሠረት ፈቃዱን ሊያስተላልፍ ይችላል ፤ ሆኖም ፈቃዱ የሚተላለፍለት ሰው በፈቃዱ የተመለከቱትን ግዴታዎች ለመወጣት የሚያስችል ብቃት ያለው መሆን አለበት ።

፲፯· ፈቃድ ስለማሻሻል

ማንኛውም ባለፈቃድ ፈቃዱን ለማሻሻል ከፈለገ ለኤጀንሲው በጽሁፍ ያመለክታል ። በማመልከቻው ላይም የዚህ ክፍል ምዕራፍ ሁለት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ ።

፲፰· ስለፈቃድ ዘመንና እድሳት

፩· በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት የሚሰጥ ፈቃድ ጸንቶ የሚቆይበት ዘመን በፕሮጀክቱ ዕድሜ ላይ የተመሠረተ ሆኖ ጣሪያው እንደሚከተለው ይሆናል ፤

ሀ) ለኃይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ፈቃድ .................................... ፵ ዓመት

ለ) ለኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ፈቃድ .................................... ፶ ዓመት

ሐ) ለኤሌክትሪክ ኃይል ማከፋፈልና መሸጥ ፈቃድ .................................... ፶ ዓመት

2) Where an objection to the application has been filed pursuant to Article 11 of these Regulations, the granting of license shall be deferred pending a decision by the Agency within 120 days from the registration. If the decision of the Agency is against the submitted objection, then, a license shall be issued to the the applicant subject to sub-article (1) of this Article.

3) No license shall be issued under these regulations unless the applicant is eligible to invest in the sector pursuant to the provisions of the relevant investment law.

14. *Refusal of License*

1) If the Agency determines that the application or the information supplied or the qualifications, experience or financial capacity of the applicant in connection with the proposed license is materially inadequate, it shall so notify the applicant in writing setting the reasons of the decision.

2) The applicant shall be permitted to consult with the Agency in order to provide all evidence in support of his position, shall be afforded a time not less than 30 days to overcome the objection of the Agency, and shall also be entitled to amend or complete his application.

3) If, following such consultation and expiry of such time, the Agency still believes that the application or the information supplied or the qualifications of the applicant are materially inadequate to justify the grant of a license, it shall notify same to the applicant in writing.

15. *Replacement and Issuance of Copies of Licenses*

1) The licensee may, upon the payment of the prescribed fees, request the Agency to issue one or more copies of his license. Upon receiving such request, the Agency shall issue such certified copies to the licensee.

2) The licensee may, upon the payment of the prescribed fees, apply to the Agency for the replacement of his license which has been lost or destroyed. Upon receiving such application the Agency shall issue replacement of such license to the licensee.

16. *Transfer of License*

Any licensee may transfer his license pursuant to Article 12 of the Proclamation; provided, however, that the transferee has the required competence to fulfill the obligations of the license.

17. *Amendment of License*

If a licensee desires any amendment to be made to his license, he shall submit a written application to the Agency. Such application shall also be subject to the provisions of Chapter Two of this Part.

18. *Duration and Renewal of License*

1) The duration of a license issued pursuant to the provisions of the Proclamation and these Regulations shall be based on the life of the project; provided, however, that the maximum duration shall not exceed the following:

(a) for hydro power generation license .................................... 40 years

(b) for transmission license ............... 50 years

(c) for distribution and sale license .... 50 years

መ) ለኤሌክትሪክ አስመጪነት ወይም ላኪነት ፈቃድ .................................... ፲ ዓመት

፪· ከኃይድሮ ውጭ ለሌሎች ኃይል ማመንጫዎች የፈቃድ ዘመን ጣሪያ በሚኒስቴሩ በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል ።

፫· ማናቸውም ባለፈቃድ ፡

ሀ) የፈቃዱ ዘመን ከማለቁ ሁለት ዓመት በፊት ፈቃዱ እንዲታደስለት ከጠየቀ ፡

ለ) የአዋጁን ፡ የዚህን ደንብና በእነዚሁ መሠረት የሚወጡ መመሪያዎችን በመተላለፍ ፈቃዱን ለመሰረዝ የሚያበቃ ጥፋት ካልፈጸመ ፡ እና

ሐ) የሥራውን ደረጃ የኤሌክትሪክ ኢንዱስትሪ በወቅቱ በደረሰበት ዘመናዊ ቴክሎኖሎጂና አጠቃላይ ተቀባይነት ባለው የአሠራር ልምድ ለማሳደግ ከተስማማ ፡

ፈቃዱ በተከታታይ ሊታደስለት ይችላል ፤ ሆኖም እያንዳንዱ የእድሳት ዘመን ከፈቃዱ የመጀመሪያ ዘመን ግማሽ በላይ ሊሆን አይችልም ።

፬· የዚህ ክፍል ምዕራፍ ሁለት ድንጋጌዎች በፈቃድ እድሣት ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ ።

፲፱· ፈቃድን ስለመሰረዝ

የአዋጁ አንቀጽ ፲፬(፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ባለፈቃዱ ከሚከተሉት ጥፋቶች አንዱን ከፈጸመ ፈቃዱ ሊሰረዝበት ይችላል ፡

፩· የቴክኒክ ደረጃዎችን ካልጠበቀ ፣ የደኅንነት መመሪያዎችንና የአካባቢ ጥበቃ ሕጎችን ካላከበረ ፤

፪· የታሪፍ ደንቦችን ካላከበረ ፡

፫· ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ የኤሌክትሪክ አቅርቦትን በተደጋጋሚ ካቋረጠ ፣ ከቀነሰ ወይም ካቆመ ።

፳· ስለፈቃድ መቋረጥ

፩· ፈቃድ በሚከተሉት ሁኔታዎች ይቋረጣል ፤

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፰ መሠረት ሳይታደስ ከቀረ፣

ለ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፱ ድንጋጌዎች መሠረት በኤጀንሲው ከተሰረዘ ፡

ሐ) የወራሾች መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ባለፈቃዱ ከሞተ ወይም ባለፈቃዱ የንግድ ድርጅት ሲሆን ከፈረሰ ወይም የመክሰር ውሳኔ ከተሰጠበት ።

፪· ፈቃዱ ሲቋረጥ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦቱ ሳይቋረጥ እንዲቀጥል ለማድረግ የግድ አስፈላጊ የሆኑ የባለፈቃዱን የኤሌክትሪክ ተቋሞች መንግሥት ከመጽሐፍ ወይም ከመተኪያ ዋጋቸው አነስተኛ በሆነው ስሌት ላይ የተመሠረተ የካሣ ክፍያ በማሰብ ሊወስድ ይችላል ።

፫· ተቋሞቹ ከአገልግሎት ውጭ በመሆናቸው መንግሥት ሊወስዳቸው ካልፈለገ ባለፈቃዱ በራሱ ወጭ ተቋሞቹን ማስወገድ አለበት።

፳፩· ስለፈቃድ ክፍያዎች

፩· የኤሌክትሪክ ሥራ ፈቃድ ለማውጣት የሚጠይቅ ማንኛውም አመልካች የፈቃድ ማመልከቻው ሲመዘገብ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚጠየቀውን የፈቃድ ክፍያ ፳ ፐርሰንት በቅድሚያ ይከፍላል፤ ሆኖም አመልካቹ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፬ መሠረት ፈቃድ የሚከለከል ከሆነ ክፍያው አይመለስለትም።



(d) for importation or exportation license .......................................... 10 years

2) The maximum duration of license for non-hydro power generation plants shall be determined by directives of the Ministry.

3) A license may be renewed for successive periods if the licensee:

(a) has made an application to that effect two years prior to the expiry of the license;

(b) is not in breach of any provisions of the Proclamation, these Regulations and directives issued hereunder which constitutes grounds for revocation of his license; and

(c) has agreed to upgrade his operations in accordance with latest technology generally accepted in the power industry;

provided, however, that the duration of each renewal shall not exceed half of the initial period of the license.

4) Renewal shall be subject to the provisions of Chapter Two of this Part.

19. *Revocation of License*

Without prejudice to the provisions of Article 14(2) of the Proclamation, a license may be revoked when a licensee commits any one of the following infractions:

1) failure to comply with technical standards, safety requirements and environmental laws;

2) failure to comply with tariff regulations;

3) repeated interruption, reduction or termination of electricity supply in the absence of force majeure.

20. *Termination of License*

1) A license shall terminate if:

(a) it expires without being renewed pursuant to the provisions of Article 18 of these Regulations:

(b) it is revoked by the Agency pursuant to the provisions of Article 19 of these Regulations;

(c) without prejudice to the right of heirs, the licensee dies or where the licensee is not a natural person, it is liquidated or declared bankrupt.

2) Upon termination of a license, the government may take over, in consideration of compensation on the basis of book value or replacement cost whichever is the lower, the facilities of the licensee which are absolutely necessary to continue, without interruption, the supply of electric power.

3) If the government does not desire to take over the facilities due to their being unoperational, the licensee shall remove such facilities at its own cost.

21. *License Fees*

1) Any applicant for electricity operation license shall, upon the registration of his application, pay in advance 20% of the license fees to be paid under this Article; provided, however, that such payment shall not be refundable upon refusal of license under Article 14 of these Regulations.

፪· ለኤሌክትሪክ ማመንጨት ፈቃድ የሚጠየቀው ክፍያ በእያንዳንዱ ኪሎ ዋት ብር ፩ ይሆናል፤ ሆኖም ዝቅተኛው ክፍያ ብር ፩ ሺ ይሆናል።

፫· ለኤሌክትሪክ ማስተላለፍ ፈቃድ የሚጠየቀው ክፍያ በእያንዳንዱ ሰርኪዩት ኪሎ ሜትር ብር ፳ ይሆናል፤ ሆኖም ዝቅተኛው ክፍያ ብር ፪ ሺ ይሆናል።

፬· ለኤሌክትሪክ ማከፋፈልና መሸጥ ፈቃድ የሚጠየቀው ክፍያ በእያንዳንዱ ኪሎ ቮልት አምፒር የትራንስፎርመር አቅም ብር ፪ ይሆናል፤ ሆኖም ዝቅተኛው ክፍያ ብር ፩ ሺ ይሆናል።

፭· ለኤሌክትሪክ አስመጭነት ወይም ላኪነት ፈቃድ የሚጠየቅ ክፍያ በሜጋዋት ሰዓት ብር ፩ ይሆናል፤ ሆኖም ዝቅተኛው ክፍያ ብር ፪ ሺ ይሆናል።

፮· ፈቃድን ለማሻሻል ወይም ለማሳደስ የሚጠየቀው ክፍያ ለፈቃዱ ማውጫ የሚጠየቀው ክፍያ ፶ ፐርሰንት ይሆናል።

፯· ፈቃድ ለማስተላለፍ የሚጠየቀው ክፍያ ለፈቃዱ ማውጫ የሚጠየቀው ክፍያ ፳ ፐርሰንት ይሆናል።

፰· የፈቃድ ቅጅ ወይም ምትክ ለመስጠት የሚጠየቀው ክፍያ ብር ፩፻፶ ይሆናል።

## ክፍል ሦስት
## የባለፈቃዶች እና የደንበኞች ግዴታዎች

፳፪· የባለፈቃዶች መብት

ባለፈቃዶች የሚከተሉት መብቶች ይኖሯቸዋል፤

፩· የኤሌክትሪክ ሥራዎችን ለማካሄድ በፈቃዱ ወደተሸፈነው ክልል የመግባት፤

፪· የዚህን ደንብ ድንጋጌዎችና በዚህ ደንብ መሠረት የወጡ መመሪያዎችን ለሚጥሱ ደንበኞች ማስጠንቀቂያ በመስጠት የኤሌክትሪክ አቅርቦትን የማቋረጥ ፤

፫· የደንበኞችን የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን የመመርመር።

፳፫· የባለፈቃዶች ግዴታ

ባለፈቃዶች የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሯቸዋል ፤

፩· በአዋጁ ፣ በዚህ ደንብና በነዚሁ መሠረት በሚወጡ መመሪያዎች እና በፈቃዱ በተመለከቱት ግዴታዎች መሠረት የኤሌክትሪክ ሥራዎችን ማካሄድ ፤

፪· የሰውን ሕይወት ፣ የንብረትና የአካባቢን ደኅንነት ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ የጥንቃቄ እርምጃዎችን የመውሰድ ፤

፫· ለደንበኞች የማያቋርጥ የኤሌክትሪክ አገልግሎት የመስጠት ፤

፬· በፈቃዱ ክልል የሚገኙ አዲስ ደንበኞች የሚያቀርቡትን የአገልግሎት መስመር የማስቀጠል ጥያቄ በፍጥነት የማስተናገድ ፤

፭· ኤሌክትሪክ ከመቋረጡ በፊት ለደንበኞች የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ የመስጠት ፤

፮· በአዋጁ አንቀጽ ፲፮ የተመለከቱት ኤሌክትሪክ ለማቋረጥ የሚያስችሉ ምክንያቶች እንደተወገዱ የኤሌክትሪክ አገልግሎቱን ወዲያውኑ የመጀመር ፤

፯· ስለ ኤሌክትሪክ አጠቃቀም ለደንበኞች አስፈላጊውን መመሪያ የመስጠት ፤

፰· ደንበኞች ለሚያቀርቡት አቤቱታ ወዲያውኑ ምላሽ የመስጠት ፤

2) Fees to be paid for generation license shall be Birr 1.00 per kilowatt; provided, however, that minimum fees shall be Birr 1000.

3) Fees to be paid for transmission license shall be Birr 20 per circuit kilo meter; provided, however, that minimum fees shall be Birr 2000.

4) Fees to be paid for distribution and sale license shall be Birr 2 per kilo volt ampere of transformer capacity; provided, however, that minimum fees shall be Birr 1000.

5) Fees to be paid for import or export of electricity license shall be Birr 1.00 per megawatt hour; provided, however, that minimum fees shall be Birr 2000.

6) The fee to be paid for the amendment or renewal of a license shall be 50% of the fee required for the issuance of such license.

7) The fee to be paid for the transfer of a license shall be 20% of the fee required for the issuance of such license.

8) Fees to be paid for issuance of copies or replacement of license shall be Birr 150.

## *PART THREE*
## *Rights and Obligations of Licensees and Customers*

22. *Rights of Licensees*

Licensees shall have the following rights:

1) to enter the land covered by the license to undertake electricity operations;

2) to issue warnings and disconnect electricity of customers who violate any provision of these Regulations and directives issued hereunder;

3) to inspect the electricity installations of customers.

23. *Obligations of Licensees*

Licensees shall have the following obligations:

1) to carry out electricity operations in accordance with the provisions of the Proclamation, these Regulations and directives issued thereunder and the terms and conditions of the license;

2) to take proper measures in order to protect human life, property and the environment;

3) to supply electricity to customers on regular basis;

4) to respond promptly to connection demand of new customers within its license area;

5) to give advance notice to customers before each interruption of electric power;

6) to resume electricity service as soon as the reasons for the interruption stated under Article 16 of the Proclamation ceases to exist;

7) to provide customers with the necessary guidance on the use of electricity;

8) to respond promptly to customers' complaints;

፱· የቅጥር ፣ የገንዘብ ፣ የንግድና ሌሎች የሒሳብ መዛግብትና ስለኤሌክትሪክ ሥራዎች ሪኮርዶች የመያዝና በመመሪያ በሚወሰነው መሠረት በየወቅቱ ሪፖርት የማቅረብ ፣

፲· ማንኛውንም መዛግብትና ሪኮርዶችን ለኤጀንሲው ምርመራ የማቅረብ ፣

፲፩· ለኤሌክትሪክ ሥራ አስፈላጊ የሆነውን ሥልጠናና ትምህርት ለሠራተኞቻቸው የመስጠት ፣

፲፪· በዋጋቸው ተወዳዳሪና በጥራታቸው ተመጣጣኝ ደረጃ ላላቸው ፣ በሚፈለገውም መጠን ለሚገኙ የሀገር ውስጥ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ቅድሚያ የመስጠት።

፳፬· <u>የደንበኞች መብት</u>

ደንበኞች የሚከተሉት መብቶች ይኖሯቸዋል ፣

፩· ከባለፈቃዶች ያልተቋረጠ ፣ ከአደጋ የተጠበቀና ጥራት ያለው የኤሌክትሪክ አቅርቦት የማግኘት ፣

፪· የኤሌክትሪክ አገልግሎትን የሚመለከቱ አቤቱታዎችን እንደ ነገሩ አግባብነት ለባለፈቃዱ ወይም ለኤጀንሲው የማቅረብ ።

፳፭· <u>የደንበኞች ግዴታ</u>

ደንበኞች የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሯቸዋል ፣

፩· ስለኤሌክትሪክ አጠቃቀም የሚሰጡ ማስታወቂያዎችንና መመሪያዎችን የማክበር ፣

፪· የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ፣ ጥገና ፣ ምርመራና የቆጣሪ ንባብ ሥራዎች ሲካሄዱ አስፈላጊውን ትብብር የማድረግ ፣

፫· ማናቸውም የኤሌክትሪክ ብልሽት ሲያጋጥም ወዲያውኑ ለባለፈቃዱ የማሳወቅ ።

## ክፍል አራት ፣
## ስለ ኤሌክትሪክ ዋጋና ታሪፍ

፳፮· <u>አጠቃላይ መርህ</u>

፩· የኤሌክትሪክ ዋጋ አተማመን ሀብትን በብቃት በመጠቀም መርህ ላይ ተመስርቶ ተጠቃሚዎችና አምራቾች ተጨማሪ የኢነርጂ ምርትና ፍጆታ የሚያስከትለውን ትክክለኛውን የፍጆታና የማምረቻ ዋጋ በሚያገኙበት መልክ ይከናወናል ።

፪· በደንበኞች ላይ የሚጣለው የአቅርቦት ዋጋ በሲስተሙ ላይ ከሚያስከትለው የወጪ ተጽዕኖ አንፃር ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ ሆኖ የኢነርጂ አጠቃቀሙን በተቻለ መጠን ምርቱን ለማስገኘት ከሚወጣው ወጪ አንፃር ሚዛናዊ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ ይሆናል።

፫· የዋጋ ተመኑ በቂና ቀጣይነት ያለው የመዋዕለ ንዋይ ምንጭ ለማስገኘትና አስተማማኝ አገልግሎት ለማቅረብ የሚያስችል ሆኖ ፣ የአገልግሎት ብቃትን ለማሻሻል የሚያስችል የዋጋ አተማመን ሥርዓት መያዝ አለበት ።

፬· ዝርዝር የታሪፍ መደቦች አወጣጥ የአፈጻጸም ችግሮችን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ እንዲያስችል በተቻለ መጠን ያልተወሳሰበ እንዲሆን ይደረጋል ።

፳፯· <u>የዋጋ አተማመን አጠቃላይ ስልቶች</u>

፩· ለጅምላም ሆነ ለችርቻሮ ተጠቃሚዎች የኢነርጂና የኃይል አቅርቦት ዋጋ የሚተመነው ፣

ሀ) በሲስተሙ ላይ የተወሰነ ተጨማሪ ኃይል ወይም ኢነርጂ ለማመንጨት በሚደረገው ወጪ ፣ እና



9) to keep all employment, financial, commercial and other books and records as well as records of electricity operations, and submit reports periodically as determined by directives;

10) to make available to the Agency all books and records for inspection;

11) to give employees the training and education necessary for electricity operations;

12) to give preference to domestic goods and services, where they are readily available at competitive price and are of comparable quality.

24. *Rights of Customers*

Customers shall have the following rights:

1) to require the provision of regular, safe and quality electricity services from licensees;

2) to submit to the licensee or the Agency,as may be appropriate, any complaints related to electricity services.

25. *Obligations of Customers*

Customers shall have the following obligations:

1) to comply with notices and instructions on the use of electricity;

2) to facilitate the installation, repair, inspection and meter reading of electricity;

3) to promptly notify the licensee of any irregularities of electricity.

## *PART FOUR*
## *Electricity Price and Tariff*

26. *General Principles*

1) Electricity pricing shall be based on the principle of efficient allocation of resources where customers and producers receive the true costs associated with consuming and producing one additional unit of energy respectively.

2) The price that customers get charged for shall be computed in consideration of the cost incurred by the total system, and the energy consumption shall, as much as possible, be made fair taking the production cost into account.

3) The rate level shall be made sufficient enough to support continuing investments and sustainable services, and shall include a system of pricing that guarantees an improved service efficiency.

4) Tariff structures shall be kept simple enough to avoid or minimize implementation difficulties.

27. *General Pricing Approach*

1) Price for supplying energy and power to retail or bulk customers shall, subject to adjustments to meet financial requirements to be defined as necessary, be determined on the basis of:

(a) the system marginal cost; and

ለ) በሲስተሙ የከፍተኛ ውጤታማነት ዕቅድ ፣ ላይ የተመሠረተ ሆኖ አስፈላጊ ነው ተብሎ በሚወሰነው ገደብ የፋይናንስ ፍላጎትን ሊያሟላ በሚችል መልኩ ሊስተካከል ይችላል ።

፪· ከብሔራዊ ግሪድ ውጭ ለሚደረግ የዋጋ አተማመን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ስልት በቴክኒካዊ ምክንያት ተግባራዊ ሊሆን የማይችል ሲሆን የአቅርቦት ዋጋ አተማመኑ ፣

ሀ) በአማካይ የአቅርቦት ዋጋ ፣ እና

ለ) ተቀባይነት ባለው የትርፍ መጠን ፣

ላይ ይመሠረታል ።

፳፰· <u>የማመንጫ ዋጋ አተማመን</u>

፩· በብሔራዊ ግሪድ ሲስተም ውስጥ የኃይል ማመንጫ ዋጋ አተማመንን በሚመለከት ፣

ሀ) ማርጂናል የኃይል ማመንጫ ዋጋ የሚተመነው የሲስተሙን ከፍተኛ የኃይል ፍላጎት ለመሸፈን ይችላል ተብሎ በሚገመት ከፍተኛ ብቃት ባለው የማመንጫ ተቋም ዋጋ ላይ ተመስርቶ ይሆናል ፣

ለ) የኢነርጂ ዋጋ የሚተመነው ቋሚ የሲስተም ጭነትን ለመሸፈን ይችላል ተብሎ በሚገመተው ከፍተኛ ብቃት ባለው የማመንጫ ተቋም ዋጋ ላይ ተመስርቶ ይሆናል ፣

ሐ) ለውኃ ኃይል ማመንጫ ማርጂናል የኢነርጂ ዋጋ የሚተመነው ከአጠቃላይ ወጪው ላይ የኃይል አቅርቦት ዋጋ ተቀንሶ በሚቀረው ዋጋ ላይ በመመስረት ይሆናል ።

መ) በነዳጅ የሚንቀሳቀስ የኃይል ማመንጫ ወጪ እንዲሁም በጅምላ ግዥ የሚገኝ የኃይልና የኢነርጂ ዋጋ በማመንጨት ዕቅድ ላይ በመመ ስረት ተተምኖ በሲስተሙ የማመንጨት ዋጋ ላይ ይከፋፈላል ።

፪· ከብሔራዊ ግሪድ ሲስተም ውጭ የማመንጫ ዋጋ አተማመንን በሚመለከት ፣

ሀ) ማርጂናል የማመንጫ አቅም ዋጋ የሚተመነው የገበያውን ፍላጎት ሊሸፍን በሚችል ከፍተኛ ብቃት ባለው የማመንጫ ተቋም ዋጋ ላይ ተመስርቶ ይሆናል ።

ለ) ለእያንዳንዱ የማመንጫ ተቋም ማርጂናል የኢነርጂ ዋጋ ይተመናል ፣

ሐ) ለአነስተኛ የውኃ ኃይል ማመንጫ ተቋማት እንደ አግባብነቱ በብሔራዊ ግሪድ ሲስተም ውስጥ ላሉት ለከፍተኛ የውኃ ኃይል ማመንጫ ተቋማት የሚሠራበት የዋጋ አተማመን ሊወሰድ ይችላል ፣

መ) ለየማመንጫው የተተመነው ዋጋ በአቅርቦት ክልል ውስጥ ለማመንጨት በታቀደው የኢነርጂ መጠን አኳያ በአቅርቦቱ አጠቃላይ ዋጋ ላይ እንዲበተን ይደረጋል ፣ ይህ ዋጋ እንደአስፈላጊነቱ በየጊዜው በኤጀንሲው ይገመገማል ፣

(b) optimum system planning.

2) Where the approach stated under Sub-Article (1) of this Article becomes inapplicable to pricing outside the national grid system due to technical reasons, such pricing shall be based on:

(a) average cost of supply; and

(b) an acceptable rate of return on investment.

28. Generation Pricing

1) With regard to generation pricing within the national grid system:

(a) the most efficient generation facility identified to meet the system's peak demand shall constitute the base for marginal generation capacity cost;

(b) the most efficient generation facility identified to meet the system's base load shall provide the base for computation of energy price;

(c) marginal energy cost shall, in the case of hydro power plants, be computed on the basis of the cost which is not attributed to capacity;

(d) generation cost of thermal plants and wholesale purchase price of power and energy shall be computed on the basis of planned generation and shall be distributed on the system generation price.

2) With regard to generation pricing outside the national grid system:

(a) the most efficient generation facility used to meet the system demand shall constitute the base for determining the marginal generation capacity cost;

(b) marginal energy cost shall be computed for each generation facility;

(c) for cases of small hydro power plants similar approach may be used as in the case of large hydro power plants in the national grid system;

(d) generatorss' specific prices shall be spread over the system generation price on the basis of planned generation within the system; and, where appropriate, frequent review of such price by the Agency shall be maintained.

ሠ) በነዳጅ ኃይል የሚሠሩ የኃይል ማመንጫዎች በበቂ ደረጃ የሚገኙበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የሚያስችል ተገቢ የማበረታቻና የመቅጫ ስልቶች በዋጋ አተማመኑ እንዲካተቱ ይደረጋል።

፫· ከግል አምራቾች በጅምላ የሚገዛ ኃይልና ኢነርጂ ዋጋ ኤጀንሲው በሚያጸድቀው የግዢ ውል መሠረት የሚተመን ሆኖ ወደ ተጠቃሚ ደንበኞች በቀጥታ የሚተላለፍ ይሆናል።

፳፱· የኃይል ማስተላለፊያ ዋጋ አተማመን

፩· በብሔራዊ ግሪድ ሲስተም ውስጥ የኃይል ማስተላለፊያ ዋጋ አተማመንን በሚመለከት ፤ የሲስተም ማርጅናል ማስተላለፊያ አቅም ዋጋ ለማስተላለፊያ ዋጋ አተማመን መሠረት ይሆናል።

፪· ከብሔራዊ ግሪድ ሲስተም ውጭ የኃይል ማስተላለፊያ ዋጋ አተማመንን በሚመለከት ፤ የሲስተሙ የኃይል ማስተላለፊያ ዋጋ የሚተመነው በሂሣብ አያያዝ በተደረሰበት ግምታዊ ወይም የተረጋገጠ ወጪ እና ተቀባይነት ባለው የትርፍ መጠን ላይ ተመስርቶ ይሆናል ።

፴· የኃይል ማከፋፈያ ዋጋ አተማመን

፩· በብሔራዊ ግሪድ ሲስተም ውስጥ የኃይል ማከፋፈያ ዋጋ አተማመንን በሚመለከት ፤ የሲስተም ማርጅናል የማከፋፈል አቅም ዋጋ ለማከፋፈያ ዋጋ አተማመን መሠረት ይሆናል ።

፪· ከብሔራዊ ግሪድ ሲስተም ውጭ የኃይል ማከፋፈያ ዋጋ አተማመንን በሚመለከት ፤ የሲስተሙ የኃይል ማከፋፈያ ዋጋ የሚተመነው በሂሣብ አያያዝ በተደረሰበት ግምታዊ ወይም የተረጋገጠ ወጭ እና ተቀባይነት ባለው የኢንቨስትመንት ምላሽ መጠን ላይ ተመስርቶ ይሆናል ።

፫· በደንበኞች ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው ታሪፍ የሚወሰነው በሚጠቀሙበት ቮልቴጅ ደረጃ ተሰልቶ በሚገኘው የማከፋፈያ ወጪ ላይ የማመንጫና የማስተላለፊያ ወጪዎች ተደምረውበት ይሆናል ።

፴፩· ሌሎች ክፍያዎች

፩· የኃይልና ኢነርጂ ቆጣሪ ወጪዎችና የኤሌክትሪክ ፍጆታ ክፍያን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ወጪዎች ለደንበኞች አገልግሎት ዋጋ አተማመን መሠረት ይሆናሉ ።

፪· የማስቀጠያ ክፍያ አዲስ የኃይል ጥያቄን ለደንበኛ ለማቅረብ በሚያስፈልገው ተጨማሪ ወጪ ላይ የሚመሠረት ይሆናል ።

፫· የሪአክቲቭ ፍጆታ ክፍያ ፍጆታው በሚፈጸምበት ቮልቴጅ ደረጃ የእያንዳንዱ የሪአክቲቭ ፍጆታ ከሚፈጥረው የተጨማሪ አቅም ዋጋ ጋር እንዲገናዘብ ይደረጋል ።

፬· ሌሎች እንደአስፈላጊነቱ የሚፈጸሙ ክፍያዎች በባለፈቃዶችና በደንበኞች መካከል የሚደረጉ ስምምነቶችን መሠረት በማድረግ ይፈጸማሉ ።

፴፪· ስለ አሠራር ብቃት መለኪያዎችና ስለዋጋ ትመና ሥርዓት

፩· የኤሌክትሪክ አቅርቦትን የማሻሻል ዕድሎችን ለመጠቆሚያነት የሚያገለግሉና በአቅርቦት ዋጋዎች ላይ ተጽዕኖ ሊያስከትሉ የሚችሉ የማመንጫ ፣ የማስተላለፊያና የማከፋፈያ የአሠራር ብቃት መለኪያዎችን ኤጀንሲው ከባለፈቃዶች ጋር በመመካከር ይወስናል ።

(e) appropriate incentive and penalty mechanisms shall be incorporated in the pricing process for securing a higher level for availability of thermal generation facilities.

3) Price of bulk energy and power from private producers shall be determined in accordance with power purchase agreements as approved by the Agency, and shall be directly transferred to customers.

29. Power Transmission Pricing

1) The system marginal transmission capacity cost shall form the base for transmission pricing within the national grid system.

2) The system's transmission capacity cost outside the national grid system shall be determined on the basis of estimated or actual accounting costs and an acceptable rate of return on investment.

30. *Power Distribution Pricing*

1) With regard to power distribution pricing within the national grid system, system marginal distribution capacity cost shall form the base for distribution pricing.

2) With regard to power distribution pricing outside the national grid system, the system's distribution capacity cost shall be determined on the basis of estimated or actual accounting costs and an acceptable rate of return on investment.

3) Generation and transmission costs at the appropriate voltage level shall be added on top of the distribution cost to form the tariff applicable to customers.

31. Other Charges

1) Energy and power metering costs and billing costs shall form the base for determining marginal customer related costs.

2) Payment of connection charges shall be related to additional costs resulting from supplying new demand.

3) Charges on reactive power consumption shall be related to the capacity cost that each reactive power consumption entails at the voltage level at which the consumption is effected.

4) Other appropriate charges may be effected in accordance with contractual agreements between licensees and customers.

32. *Efficiency Indexes and Pricing Procedures*

1) The Agency shall, in consultation with licensees, determine generation, transmission and distribution efficiency indexes indicating potentials for improving electricity services which would have ultimate bearing on prices.

፪· አግባብነት ያላቸውን የዋጋ መተመኛ መስፈርቶች ሁሉ አቀናጅቶ በመጠቀም የዚህን ክፍል ድንጋጌዎች ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ዝርዝር የዋጋ ትመና ሥርዓት በኤጀንሲው ይወሰናል ።

፴፫· <u>ስለዋጋ ወቅታዊ ማስተካከያዎችና ስለታሪፍ ክለሳ ጥናቶች</u>

፩· የማመንጫ ፡ የማስተላለፊያና የማከፋፈያ ዋጋ ወቅታዊ ማስተካከያዎች ከሚመለከታቸው የምርት ግብአቶች ዋጋ ለውጥና ከአሠራር ብቃት መለኪያዎች አኳያ ይደረጋሉ ።

፪· የዋጋ ወቅታዊ ማስተካከያ የሚደረግበት የጊዜ ገደብ በኤጀንሲው ይወሰናል ።

፫· አጠቃላይ የታሪፍ ክለሳ ጥናት በየአራት ዓመቱ ይካሄዳል።

፴፬· <u>ስለሂሣብ መዝገብ አያያዝ</u>

፩· ተቀባይነት ካላቸው የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት አጠቃላይ መርሆች ጋር የተጣጣመና የዋጋ ቁጥጥር ሥርዓቱን ለመደገፍ የሚችል ሆኖ በባለፈቃዶች ሥራ ላይ የሚውል አንድ ወጥ የሆነ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት በኤጀንሲው ይወሰናል ።

፪· ማንኛውም ባለፈቃድ የመንግሥት የበጀት ዓመት ባለቀ በስድስት ወራት ውስጥ በኦዲተር የተመረመረ የሂሳብ ሪፖርት ለኤጀንሲው ያቀርባል ።

<u>ክፍል አምስት</u>

<u>የደኅንነት ፡ የቴክኒክና የአገልግሎት ጥራት ደረጃዎች</u>

<u>ምዕራፍ አንድ</u>

<u>አጠቃላይ የደኅንነት መመሪያዎች</u>

፴፭· <u>ስለ ኤሌክትሪክ አቅርቦት መስመሮችና መሣሪያዎች ደኅንነት</u>

የኤሌክትሪክ አቅርቦት መስመሮችና መሣሪያዎች ፡

፩· በተዘረጉበት የአካባቢ ሁኔታዎች የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ በቂ ኃይል የመሸከምና የኢንሱሌሽን ብቃት ፡ እንዲሁም በብልሽት ወቅት ሊከሰት የሚችለውን የኤሌክትሪክ መጠን የመቋቋም ችሎታና በቂ የሜካኒካል ጥንካሬ ደረጃ ሊኖራቸው ፡ እና

፪· በሰው ፡ በእንስሳትና በንብረት ላይ ጉዳት በማያስከትል ሁኔታ ሊገነቡ ፡ ሊገጣጠሙ፡ ሊጠበቁና ሊጠገኑ ይገባል።

፴፮· <u>ከተጠቃሚዎች ጋር ስለሚገናኙ የአገልግሎት መስመሮችና መሣሪያዎች</u>

፩· ማንኛውም ባለፈቃድ በደንበኛ ግቢ ውስጥ የሚገኙና የራሱ ንብረት የሆኑ ወይም በእርሱ ኃላፊነት ሥር የሆኑ የኤሌክትሪክ አቅርቦት መስመሮች ፡ ተገጣጣሚዎችና መሣሪያዎች አደጋ በማያስከትል ሁኔታ ለአገልግሎት ብቁ ሆነው መገኘታቸውን ማረጋገጥ አለበት ።

፪· ማንኛውም ደንበኛ በግቢው ውስጥ የሚገኙ የባለፈቃዱን መሣሪያዎች በተቻለው መጠን አደጋ በማያስከትል ሁኔታ በጥንቃቄ መጠበቅ አለበት ።

፴፯· <u>ታወሮችንና ምሰሶዎችን ግራውንድ ስለማድረግ</u>

፩· የኤሌክትሪክ መስመር ተሸካሚ ባለብረት ታወሮችና ምሰሶዎች ሁሉ ከእግሮቻቸው በአንዱ ላይ ግራውንድ የማድረግ ሥራ ፳ ሚ.ሜ. ስፋት ባለው የብረት ዘንግ መከናወን አለበት ።

2) Detailed pricing procedures for applying the provisions of this Part incorporating all appropriate pricing factors shall be determined by the Agency.

33. *Interim Price Adjustments and Studies for Tariff Revisions*

1) Interim adjustments to generation, transmission and distribution prices shall be made on the basis of changes in relevant input prices and efficiency indexes.

2) The frequency of interim adjustments shall be determined by the Agency.

3) Studies on total tariff revisions shall be conducted every four years.

34. *System of Accounts*

1) Uniform system of accounts commensurate with generally accepted accounting principles and designed to support the price regulation efforts, shall be determined by the Agency to be applied by all licensees.

2) Any licensee shall submit audited reports of its accounts to the Agency within six months from the end of the Government's fiscal year.

PART FIVE

*Standards of*

*Safety, Technical and Quality of Service*

Chapter One

General Safety Requirements

35. Safety of Electrical Supply Lines and Apparatus

All electric supply lines and apparatus shall:

1) be of sufficient ratings for powers, insulation and estimated fault current and of sufficient mechanical strength for the duty which they may be required to perform under the environmental conditions of installation; and

2) be constructed, installed, protected and maintained in such a manner as to ensure safety of human beings, animals and property.

36. *Service Lines and Apparatus in Customers' Premises*

1) Any licensee shall ensure that all electrical lines, fittings and apparatus belonging to him or under his control which are in customers' premises are in safe conditions and in all respects fit for supplying power.

2) The customer shall, as far as circumstances permit, take precautions for the safe custody of the equipment in his premises belonging to the licensee.

37. *Towers and Poles Grounding*

1) All metal towers and poles shall have the basic grounding installed on one leg using ground rods with 20mm. diameter steel rods.

፪· የታወሮች ማቆሚያ የሬዚስታንስ መጠንን ወደ ፲ ኦምስ ዝቅ ማድረግ ካስፈለገ በእግሮቻቸው ላይ ተጨማሪ ግራውንድ የማድረግ ሥራ መከናወን አለበት ።

፫· ከፍተኛ ሬዚስታንስ ባላቸው ልዩ በሆኑ ድንጋያማ አካባቢዎች የታወሮች ማቆሚያ ሬዚስታንስ እስከ ፳ ኦምስ ሊደርስ ይችላል ።

፬· ከመሬት በላይ የሚዘረጉ የኤሌክትሪክ መስመሮችን የሚሸከሙ የብረት ምሰሶዎች ወይም በብረት ዘንግ የተጠናከሩ የሲሚንቶ አርማታ ምሰሶዎች እንዲሁም ከመስመሩ ጋር ግንኙነት ያላቸው የብረታ ብረት ተገጣጣሚዎች ፣ የትራንስፎርመር ኒውትራል እና የደንበኞች መቆጣጠሪያ ፓነሎች በሚያስተማምን ሁኔታ ግራውንድ መደረግ አለባቸው ።

፴፰· <u>የስዊቾችና የማቋረጫ መሣሪያዎች አቀማመጥ</u>

ከመሬት ከተገናኘ ወይም ኒውትራል ሽቦና ኤሌክትሪክ የሚተላለፍባቸውን ሽቦዎች በአንድ ላይ ለማገናኘት ወይም ለማቋረጥ ተብሎ ከተዘጋጀ የማገናኛ ስዊች በስተቀር ፣ ማንኛውም ሰርኪዩት ብሬከር ፣ ማገናኛ ወይም ስዊች ለትራንፎርመርና ጀኔሬተር ሙከራ ተግባር ለማገናኘት ወይም ጀኔሬተር ወይም ትራንስፎርመርን ለመቆጣጠር ለሚደረግ ጥናት ካልሆነ በስተቀር በማናቸውም ዓይነት ሁኔታ ከባለሁለት ሽቦ መስመሮች ወይም ከባለበርካታ ሽቦ መስመሮች ኒውትራል ወይም ከመሬት ጋር ከተገናኘ ሽቦ ጋር መገጠም የለበትም ።

፴፱· <u>ስለ መከላከያ ሽቦዎች</u>

፩· ማንኛውም የመከላከያ ሽቦ ፣

ሀ) የመበጠስ ጥንካሬ ከ፮፻፴፭ ኪሎ ግራም ማነስ የለበትም ፣

ለ) ኤሌክትሪክ መተላለፍ በሚቋረጥባቸው ቦታዎች ላይ ከመሬት ጋር መያያዝ አለበት ፣

ሐ) ብረት ወይም ስቲል ከሆነ ጋልቫናይዝድ መሆን አለበት።

፪· ማናቸውም የመከላከያ ሽቦ ወይም ተጠላልፈው የተሠሩ የመከላከያ ሽቦዎች በአደጋ ወቅት ከሽቦዎች ጋር የተገናኘው የኤሌክትሪክ መሥመር እስኪወገድ ድረስ እንዳይቀልጡ በቂ ኤሌክትሪክ የመሸከም ችሎታ ሊኖራቸው ይገባል ።

፵· <u>የቀለም ምልክቶች</u>

ባለፈቃዱ ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በማከፋፈያ ጣቢያዎች፣ በኔት ስቴሽኖችና በደንበኛው የማሠራጫ ባዝ ባሮች ላይ ከመሬት የተገናኙ ኒውትራል ሽቦዎችን ወይም ኃይል ከሚተላለፍባቸው መስመሮች ጋር የተያያዙ ሌሎች መስመሮችን መለየት በሚያስችል ሁኔታ ቋሚ የቀለም ምልክቶች ማድረግ ይኖርበታል።

፵፩· <u>ስለአደጋ መከላከያ መሣሪያዎችና መገልገያዎች</u>

፩· በማንኛውም የመንገድ አካል ወይም ሕዝብ በብዛት ሊገኝ በሚችልበት ሌላ ሥፍራ ፣ በፋብሪካ ፣ በማዕድን ሥፍራ ወይም በማናቸውም ደንበኛ ግቢ ውስጥ ከምድር በላይ የሚዘረጋ የኤሌክትሪክ መስመር ኤጀንሲው ተቀባይነት ይኖራቸዋል ብሎ ያጸደቃቸው የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎች ሊገጠሙለት ይገባል።

2) Additional basic grounding shall be installed on other legs where it is required to reduce the tower footing resistance to a maximum of 10 ohms.

3 In exceptional location of rocky soil with very high resistivity the maximum tower footing resistance may reach 20 ohms.

4) All metal supports and reinforced and pre-stressed cement concrete supports of overhead lines, metallic fittings attached thereto, neutral of transformers and control panel of customers shall be permanently and efficiently earthed.

38. *Position of Switches and Cut-out*

No cut-out, link or switch other than a linked switch arranged to operate simultaneously on the earthed or earthed neutral conductor and line conductor shall be inserted or remain inserted, in any earthed or earthed neutral conductor of a two wire system, or in any earthed neutral conductor of a multi-wire system of any conductor connected thereto except in the case of link for testing purpose or a search for use in controlling a generator or transformer.

39. *Guarding*

1) Every guard-wire shall:

(a) have an actual breaking strength of not less than 635 kg.

(b) be connected with earth at each point at which its electrical continuity is broken;

(c) be galvanized if made of iron or steel.

2) Every guard-wire or cross connected system of guard-wires shall have sufficient current carrying capacity to ensure the rendering dead, without risk of the fusing of the guard-wire or wires till the contact of any line wire has been removed.

40. *Color Coding*

Color coding of a permanent nature shall be provided by the licensee on substations, net stations and customers distribution bus bars determined by directives of the Agency to distinguish earthed neutral conductor or the conductor which is to be connected thereto from any live conductor.

41 *Productive Devices and Equipment*

1) Every overhead line erected over any part of a street, or any other public place or in any factory or mine, or in any customer's premises shall be protected with a device approved by the Agency.

፪· በደረቅና በንጹህ አሸዋ የተሞሉ የእሳት ማጥፊያ ባሊዎች፡ የእሳት ማጥፊያ መሣሪያዎችና የመጀመሪያ ዕርዳታ መስጫ ሣጥኖች ወይም መደርደሪያዎች በግልጽ ተጽፎባቸው በኤሌክትሪክ ማመንጫ ጣቢያዎች ውስጥ መቀመጥ አለባቸው።

፫· አምስትና ከዚያ በላይ ሜጋዋት የማመንጨት ችሎታ ባላቸው የኤሌክትሪክ ማመንጫ ጣቢያዎች እንዲሁም አምስትና ከዚያ በላይ ሜጋቮልት አምፒር አቅም ያላቸው ትራንስፎርመሮች ባሉባቸው የቤት ውስጥ ማከፋፈያ ጣቢያዎች ውስጥ እሳት ወይም ጢስ በሚያስ ከትል አደጋ ወቅት መጠቀም እንዲቻል በቂ ብዛት ያላቸው ጭንብሎች ግልጽ በሆነና በቀላሉ ሊደረስበት በሚችል ቦታ መቀመጥ አለባቸው።

፵፪· ስለመብረቅ መከላከያ

ለመብረቅ የተጋለጡ ከምድር በላይ የተዘረጉ የኤሌክትሪክ መስመሮች፡ የማከፋፈያ ጣቢያዎች ወይም የማመንጫ ጣቢያዎች ያሉት ማንኛውም ባለፈቃድ የመብረቅ ኤሌክት ሪክን ፍሰት አቅጣጫ ወደ መሬት የሚመሩ ብቃት ያላቸው አስተማማኝ ዘዴዎችን በጥቅም ላይ ማዋል አለበት።

፵፫· ስለአደጋ ማስጠንቀቂያ

የከፍተኛ ቮልቴጅ ኢንስታሌሽን ያለው ባለፈቃድ በአማርኛ በእንግሊዝኛና በአካባቢው ቋንቋ የተጻፈበትና የሰው የራስ ቅልና አጥንቶች አጽም ቅርጽ ያለበት የአደጋ ምልክት በጄኔሬተሮች በትራንስፎርመሮች ፡ በቀላሉ መወጣጣት በሚቻልባቸው ከምድር በላይ የተዘረጉ ምሰሶዎች እና በኤጀንሲው መመሪያ በሚወሰኑ ሌሎች ኢንስታሌሽኖች ላይ በግልጽ በሚታይና በዘላቂነት ሊቆይ በሚችልበት ሁኔታ መለጠፍ አለበት።

፵፬· ስለኤሌክትሪክ ጉዳት ማስወገጃ መመሪያ

፩· ባለፈቃዱ በኤሌክትሪክ ንዝረት ለሚጎዱ ሰዎች አስቸኳይ ዕርዳታ ለመስጠት የሚረዳ በአማርኛ ፡ በእንግሊዝኛና በአካባቢው ቋንቋ የተጻፈ መመሪያ በኤሌክትሪክ ማመንጫ ጣቢያዎች፡ በቤት ውስጥ የማከፋፈያና የመቆጣጠሪያ ጣቢያዎች እና በፋብሪ ካዎች ውስጥ ግልጽ በሆነ ቦታ ማስቀመጥ አለበት።

፪· ባለፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለ ከተው መመሪያ ቅጂ እንዲሰጠው ለሚጠይቅ ማንኛውም ሰው በኤጀንሲው መመሪያ የተወሰነውን ክፍያ አስከፍሎ ይሰጠዋል።

፫· በሰዎች በሚጠበቁ ባለከፍተኛ ቮልቴጅ ማመንጫ ጣቢያዎች ፡ በማከፋፈያ ጣቢያዎችና በመቆጣጠሪያ ጣቢያዎች ውስጥ በጥሩ ሁኔታ የሚሠሩ የሰው ሠራሽ የመተንፈሻ መሣሪያዎች ሊኖሩ ይገባል።

፵፭· ስለአደጋ ሪፖርት

ከኤሌክትሪክ ማመንጨት ፡ ማስተላለፍ ፡ ማከፋፈል ወይም መጠቀም ጋር በተያያዘ ምክንያት በተከሰተ አደጋ በሰውና በእንስሳት ላይ የደረሰን ጉዳት ወይም የሕይወት መጥፋት ወይም የንብረት ጥፋት ባለፈቃዱ ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ ፳፬ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ለኤጀንሲው ሪፖርት ማድረግ አለበት።

፵፮· አገልግሎት ስላቋረጡ የኤሌክትሪክ መስመሮች

የኤሌክትሪክ መስመሮች አገልግሎት መስጠታቸውን ካቋረጡ በኋላ ባለፈቃዱ አደጋ በማያስከትል ሁኔታ ተጠብቀው እንዲቆዩ ወይም እንዲወገዱ ማድረግ አለበት።

2) Fire buckets filled with clean dry sand, fire extinguishers and first-aid boxes or cupboards shall be conspicuously marked and kept in all generation stations, enclosed substations and switch stations.

3) Adequate number of gas masks shall be kept conspicuously at accessible places in every generation station with capacity of 5 mega watt and above and enclosed substation with transformation capacity of 5 megavolt amper and above for use in the event of fire or smoke.

42 *Protection Against Lightening*

Any licensee owning overhead line, substation or generation station, which is so exposed as to be liable to injury from lightening shall adapt efficient means for diverting to earth any electrical surges due to lightening.

43 *Danger Notice*

Any licensee owning high voltage installation shall affix permanently in a conspicuous position a danger notice in English, Amharic and the local language of the area with the sign of skull and bones on generators, transformers, supports of overhead lines which can be easily climbed and other electrical installations as may be required by directives of the Agency.

44 *Instructions for Restoration from Electric Shock*

1) Instructions in English, Amharic and the local language of the area for the restoration of persons suffering from electric shock shall be affixed by the licensee on a conspicuous place in every generation station, enclosed substation, enclosed switch station and in every factory.

2) Copies of the instructions referred to in sub-article (1) of this Article shall be supplied on demand by any person at a price to be fixed by directives of the Agency.

3) In every manned high voltage generation station, substation or switch station, an artificial respirator shall be provided and kept in good working condition.

45 *Accident Report*

If any accident occurs in connection with generation, transmission, distribution or use of electrical energy resulting in injury or loss of human or animal life or damage to property, the licensee shall send to the agency a report on the accident within 24 hours of knowledge of its occurrence.

46 *Unused Overhead Lines*

Where an overhead line ceases to be used as an electrical supply line, the licensee shall maintain it in a safe mechanical condition or remove it.

፵፯· ክልከላዎች

፩· አምፖሎችን፣ ፋኖችን፣ ፊውዞችን፣ ማብሪያ ማጥፊያ ዎችን፣ የዝቅተኛ ቮልት የቤት ውስጥ የኤሌክትሪክ ቁሳቁሶችንና ተገጣጣሚዎችን ከመለወጥ በስተቀር በማገልገል ላይ ባለ የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን ላይ በመጨመር፣ በመቀየር፣ በመጠገን ወይም በማስተ ካከል የኃይል ብቃቱን ወይም ባህሪውን የሚቀይሩ ሥራዎችን ከባለፈቃዱ ውጭ ወይም በባለፈቃዱ ስምምነትና በኤሌክትሪክ ሥራ ተቋራጭ ከሚሠራው ውጭ በደንበኞቹ ግቢ ውስጥ ማከናወን የተከለከለ ነው።

፪· ከመሬት በላይ በተዘረጋ የኃይል መስመር ሥር ወይም መጠበቅ በሚገባው የጎን ርቀት ክልል ውስጥ ግንባታ ማከናወን ወይም ዛፎችን ማሳደግ የተከለከለ ነው።

፵፰· የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽኖችን ስለመመርመርና ስለመፈተሽ

ኤጀንሲው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የኤሌክትሪክ ማመንጫ ጣቢያዎችን፣ የማከፋፈያ ጣቢያዎችን፣ የማስተላ ለፊያ መስመሮችን፣ የመቆጣጠሪያ ጣቢያዎችንና ሌሎች የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽኖችን በማናቸውም ጊዜ ሊመረ ምርና ሊፈትሽ ይችላል።

ምዕራፍ ሁለት

ስለማስተላለፊያ መስመሮችና ማከፋፈያ ጣቢያዎች

፵፱· የኤሌክትሪክ መስመር አቋርጦ ስለሚያልፍባቸው ሥፍራዎች

የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ መስመር አቋርጦ የሚያል ፍባቸው ሥፍራዎች በሚመረጡበት ወቅት የሚተላለፈው የኤሌክትሪክ ጭነት መጠንና ባህርይ፣ የኃይል ምንጩ አስተማማኝነት፣ የማከፋፈያ ጣቢያዎች አቀማመጥ፣ የአቅ ርቦት የወደፊት መስፋፋት ዕድል ፣ የደኅንነትና የአካባቢ ተጽዕኖዎች እንዲሁም የግንባታና የሥራ ማስኬጃ ወጪዎች ከግምት ውስጥ መግባት አለባቸው።

፶· ስለማስተላለፊያና የመከላከያ ሽቦዎች

፩· የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ሽቦዎች የሚጠበቅባ ቸውን የኤሌክትሪካል ፣ መካኒካልና፣ ኢኮኖሚያዊ መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው ።

፪· የሽቦዎቹ መጠን የሚመረጠው በብሔራዊ ደረጃዎች ወይም ብሔራዊ ደረጃዎች ከሌሉ በኢንተርናሽናል ኢሌክትሮ ቴክኒካል ኮሚሽን ደረጃዎች ተስማሚነት ካላቸውና በደረጃዎቹ መስፈርቶች ከሚታቀፉት መካከል ይሆናል።

፫· የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) በመከተል የሚደረገው ምርጫ የኤጀንሲውን አጠቃላይ መመሪያ መሠረት አድርጎ መፈጸምና የተመረጡትን ሽቦዎች ኤሌክትሪክ የመሸከም ችሎታ፣ የኮሮናንና የሬዲዮ ጫጫታ የማስወገድ ብቃት፣ ቮልቴጅ የመቀነስ ሁኔታና ሌሎች ቴክኒካዊ ጠባዮች በመፈተሽ መታገዝ አለበት።

47 *Prohibitions*

1) No electrical installation work including additions, alterations, repairs and adjustments to existing installation, except such replacements of lamps, fans, fuses, switches, low voltage domestic appliances and fittings as in no way alter its capacity or character, shall be carried out in the premises of the customer except by the licensee or an electrical contractor with the consent of the former.

2) Undertaking any type of construction work or growing trees shall not be allowed under electric power lines or within the distance of horizontal clearance thereof.

48 *Inspection and Testing of Electrical Installation*

The Agency may, where it deems it necessary and at any time, inspect and test generation stations, substations, transmission lines, switch stations and other electrical installations.

CHAPTER TWO

*Transmission Lines and Substations*

49. *Line Route*

In the process of line route selection, size and character of load, reliability of power sources, positions of substations, future expansion possibilities, safety and environmental impacts as well as construction and operational costs shall be taken into consideration.

50. *Conductors and Earth Wires*

1) Conductors shall satisfy all electrical, mechanical and economical requirements.

2) The cross section of conductors shall normally be selected from the suitable national standard ranges or where such standard is not available from that of the International Electro-Technical Commission standards.

3) The selection under Sub-Article (1) and (2) of this Article shall be carried out in accordance with guidelines of the Agency and shall be followed by checks for current carrying capacity, corona and radio noise elimination, mechanical strength, voltage drop and other factors.

፶፩. ስለኢንሱሌተሮች

፩. ለተለያዩ መሣሪያዎች፡ ዕቃዎች ፡ ስትራክቸሮች የሚያስፈልገው የኢንሱሌሽን ደረጃ የሚመረጠውና ሥራ ላይ የሚውለው የኢንሱሌተሮች ብልሽትና የአገልግሎት መቋረጥ ብዛት በኢኮኖሚያዊ መመዘኛ የተቀባይነትን ደረጃ ማሟላት እንዲችል ለማድረግ የኦቨር ቮልቴጅ መጠንና መስመሩን ከአደጋ ለመከላከል የተገጠሙትን ልዩ ልዩ መሣሪያዎች ጠባያት ከግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል።

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚደረገው ምርጫ በብሔራዊ ደረጃዎች ወይም ብሔራዊ ደረጃዎች ከሌሉ በኢንተርናሽናል ኤሌክትሮ ቴክኒካል ኮሚሽን ደረጃዎች መሠረት ይፈጸማል።

፶፪. ስለተገጣጣሚዎች

ቦል አይና ሶኬት ካፕሊንግ፡ የኮሻክልስ፡ ክላምፕስ ፡ አርኪንግ ሆርን፡ ቫይብሬሽን ዳምፐርና አርመር ሮድን የሚያካትቱ፡ የቅጥልጥል ስኒዎች ተገጣጣሚዎች እንደ ቮልቴጅ መጠናቸው የብሔራዊ ደረጃዎችን ወይም ብሔራዊ ደረጃዎች ከሌሉ የኢንተርናሽናል ኤሌክትሮ ቴክኒካል ኮሚሽን ደረጃዎችን በጠበቀ ሁኔታ መመረጥ አለባቸው።

፶፫. የፌዝ ሽቦዎችን ቦታ ስለመቀያየር

የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ የፌዝ ሽቦዎችን ቦታ የመቀያየር ተግባር ለአጫጭር ርዝመት መስመሮች ከሆነ በየመካከሉ በሚገኙ የማከፋፈያ ጣቢያዎች፡ ለባለ ፩፻፴፪ ኪሎ ቮልትና ከዚያ በላይ ለሆኑ ረጃጅም መስመሮች ከሆነ እንደ ፌዞቹ አቀማመጥ አመቺ በሆነ ቦታ ላይ መከናወን ይኖርበታል።

፶፬. ስለታወሮች ዲዛይን

፩. የከፍተኛ ቮልቴጅ ማስተላለፊያ ታወሮች የኤሌክትሪክ መስመሩ ይኖረዋል ተብሎ በሚገመተው ዕድሜ ወቅት ሊከሰቱ የሚችሉትን የሚከተሉትን ሸክሞች መቋቋም በሚችሉበት ሁኔታ ዲዛይን መደረግ አለባቸው፣

ሀ) የነፋስን ግፊት፡ የማስተላለፊያና የመከላከያ ሽቦዎችንና የቅጥልጥል ሲኒዎችን ክብደትና የሽቦዎችን ውጥረት፣

ለ) በማስተላለፊያና መከላከያ ሽቦዎች መበጠስ ሳቢያ የሚከሰቱ የመዝመምና የመጠምዘዝ እንቅስቃሴዎች የሚያስከትሉትን ጭነት፣

ሐ) በግንባታና በጥገና ሥራ ወቅት ሊከሰቱ የሚችሉ ጭነቶችን።

፪. የሽቦዎች ጥንካሬ የሚሰላው በማንኛውም ጊዜ ሊከሰት የሚችለውን የአየር ሙቀትና ቅዝቃዜ መጠንና የንፋስ ፍጥነት ከግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል።

፫. የታወር መጠን በሚተመንበት ጊዜ በፌዞች መካከል፡ በፌዞችና በሌሎች አካሎች መካከልና ከመሬት የሚኖረው የኤሌክትሪክ መስመር ርቀት፡ የቅጥልጥል ስኒዎች ርዝመት እና የርግበትና የሺልድ መከላከያ ሽቦ አንግል ከግምት ውስጥ መግባት አለባቸው።

51. *Insulators*

1) The insulation levels of different devices, equipment or structures shall be selected and applied taking into account the over voltage magnitudes in the network as well as the properties of different protective means so that the number of insulation failures and operational outages are limited on an acceptable economical level.

2) The selection under Sub-Article (1) of this Article shall comply to the national standard or where such standard is not available to the International Electro-Technical Commission standards.

52. *Fittings*

String insulator fittings of ball eye and socket couplings, yokeshackels, clamps, arcing horns, vibration dampers and armor rods shall be selected according to their voltage in conformity with the national standard or where such standard is not available with the International Electro–Technical Commission standards.

53. *Line Transposition*

The transposition of short lines shall be at intermediate substations and that of long lines shall be at suitable points along the line for voltage 132 kv and above depending on circuit arrangements.

54. *Designs of Towers*

1) Towers shall be designed to withstand the following loads which are assumed to occur during the estimated life time of the line:

(a) wind loads, weights of conductors, earth-wires and insulator strings and conductor tensions;

(b) the overturning and torsional movements resulting from the breakdown of any one of the conductors and earth-wires;

(c) loads to be caused by erection and maintenance works.

2) The conductor forces shall be calculated in all assumed temperatures and wind velocities.

3) In determining the dimensions of a tower, phase to phase, phase to body and ground clearances, length of insulator strings and maximum sag and shielding angle shall be considered.

፬· የታወር መሠረት ዲዛይኖች በመደበኛ አገልግሎት ወቅት ከሚኖረው ጭነትና ከሽቦዎች መበጠስ ሁኔታ፣ በእያንዳንዱ እግር የሚከሰተውን የአፕሊፍትና ኮምፕሬሽን ኃይል ከመቋቋምና አግባብነት ካላቸው የደኅንነት መስፈርቶች አንጻር መታየት ይኖርባቸዋል።

፭· የታወር ዲዛይን እንደአግባቡ የወደፊት ኃይል የማስተላለፍ ፍላጎት ዕድገትን በማገናዘብ መሠራት አለበት።

፶፭· <u>ኃይል በሚተላለፍባቸውና በማይተላለፍባቸው አካላት መካከል መጠበቅ ስለሚገባው ርቀት</u>

የኤሌክትሪክ ኃይል በሚተላለፍባቸውና ከመሬት ጋር በተገናኙ ኃይል በማይተላለፍባቸው አካላት መካከል መኖር የሚገባው ዝቅተኛ ርቀት በኤጀንሲው መመሪያ መሠረት ይወሰናል።

፶፮· <u>በፌዞች መካከል መጠበቅ ስለሚገባው ርቀት</u>

በኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ወይም በመከላከያ ሽቦዎች መካከል መጠበቅ የሚገባው ርቀት የሚወሰነው በከፍተኛ ሙቀት ወቅት ሽቦዎች የሚኖራቸውን የርግበት መጠን የቅጥልጥል ሲኒዎችን ርዝመት ከግምት ውስጥ በማስገባትና ኤጀንሲው የወሰነውን ስታንዳርድ በመከተል ይሆናል።

፶፯· <u>ከምድር፣ ከመንገዶችና ለመጓጓዣነት ከሚያገለግሉ የውኃ አካላት መጠበቅ ስለሚገባው ርቀት</u>

፩· የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ሽቦዎች፣ ኃይል በሚተላለፍባቸውና በማይተላለፍባቸው አካላት መካከል ሊኖር ከሚገባው ዝቅተኛ ርቀት በተጨማሪ፣ በከፍተኛ የአየር ሙቀት ወቅት ከምድር ወይም ከውኃ ወለል በላይ ቢያንስ የ፭ ሜትር ከፍታ ሊኖራቸው ይገባል።

፪· የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ሽቦዎች ከመንገድ ወለል በላይ ሊኖራቸው የሚገባው ከፍታ፣

ሀ) በከፍተኛ የአየር ሙቀት ወቅት ከ፰ ሜትር፣ እና

ለ) በአጎራባች ታወሮች ላይ የተወጠሩ ሽቦዎች በሚበጠሱበት አጋጣሚ መጠበቅ የሚገባው ርቀት ከ፯ ሜትር ማነስ የለበትም።

፫· በካናሎችና በሌሎች ለመጓጓዣነት ከሚያገለግሉ የውሃ አካሎች በላይ የሚዘረጉ የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ሽቦዎች ኃይል በሚተላለፍባቸውና በማይተላለፍባቸው አካላት መካከል ሊኖር ከሚገባው ዝቅተኛ ርቀት በተጨማሪ ፣ በከፍተኛ የአየር ሙቀት ወቅት በከፍተኛው የውኃው አካል ላይ ከሚንቀሳቀሰው ማጓጓዣ ከፍተኛ ምሰሶ ጫፍ በላይ ቢያንስ የ፩·፭ ሜትር ከፍታ ሊኖራቸው ይገባል።

፶፰· <u>ከሕንጻዎችና ግንባታዎች መጠበቅ ስለሚገባው ርቀት</u>

፩· የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ሽቦዎች በከፍተኛ ንፋስ ወቅት ከማንኛውም የሕንጻ ወይም የግንባታ አካል ቢያንስ ፬·፭ ሜትር የጎን ርቀት ሊኖራቸው ይገባል ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገውን ሁኔታ ማሟላት የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ የኃይል ማስተላለፊያ ሽቦዎቹ ከሕንጻው ወይም ከግንባታው ጫፍ በላይ የሚኖራቸው ከፍታ በከፍተኛ የአየር ሙቀት ወቅት እንዲሁም በአጎራባች ታወሮች ላይ የተወጠሩ ሽቦዎች በሚበጠሱበት አጋጣሚ መጠበቅ የሚገባው ርቀት ቢያንስ ፭·፭ ሜትር መሆን አለበት ።

4) The designs of foundations shall be checked for uplift and compression forces in each tower footing arising from normal working, loading, and broken wire conditions with the appropriate factor for safety.

5) The designs of towers shall, as may be appropriate, consider future growth in the demand for power transmission.

55. *Clearance between Line and unenergized Parts*

The minimum distance between the unenergized, earthed, and live parts of the line shall be determined in accordance with directives of the Agency.

56. *Clearance between Phases*

The minimum spacing between the conductors or earth wires shall be determined by taking into consideration sag of the conductor at maximum temperature, length of the suspension insulator string, and the standard set by the Agency.

57. *Clearance from Terrain, Roads and Water Ways*

1) The height of conductors, at maximum temperature, above ground or water surface shall be at least 5 meters plus the minimum distance between live and unenergized parts.

2) The height of conductors from the road surface shall be at least:

(a) 8 meters at maximum temperature; and

(b) 7 meters with conductor broken in the neighboring span.

3) In canals and other navigable water ways, the height of conductors from the highest mast shall, at the highest water level and at maximum temperature, be at least 1.5 meters plus the minimum distance between live and unenergized parts.

58. *Clearance from Buildings and Structures*

1) The horizontal distance from conductors to any point of a building or structure shall, with maximum wind, be at least 4.5 meters.

2) If the requirement stated under Sub-Article (1) of this Article cannot be fulfilled, the height of the conductor from the building or structure shall, at maximum temperature and with conductor broken in the neighboring span, be at least 5.5 meters.

## ፶፱· ከዛፎች መጠበቅ ስለሚገባው ርቀት

፩· የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ሽቦዎች ፡ ኃይል በሚተላለፍባቸውና በማይተላለፍባቸው አካላት መካከል ሊኖር ከሚገባው ዝቅተኛ ርቀት በተጨማሪ ፡ በከፍተኛ የአየር ሙቀትና በከፍተኛ ንፋስ ወቅት ከዛፎች ሊኖራቸው የሚገባው የከፍታና የጎን ርቀት ቢያንስ ፩.፭ ሜትር መሆን አለበት ።

፪· የፍራፍሬ ዛፎች ሲሆኑ ፡ ኃይል በሚተላለፍባቸውና በማይተላለፍባቸው አካላት መካከል ሊኖር ከሚገባው ዝቅተኛ ርቀት በተጨማሪ ፡ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተደነገገው መሠረት መኖር ያለበት ርቀት ፬ ሜትር ይሆናል ።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተመለከቱት ርቀቶች የሚወሰኑት ዛፎቹ ይኖራቸዋል ተብሎ የሚገመተውን የእድገት መጠን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ይሆናል ።

## ፷· ከሌሎች መስመሮች መጠበቅ ስለሚገባው ርቀት

፩· ጎን ለጎን የተዘረጉ መስመሮችን በሚመለከት በኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ሽቦዎችና በሌሎች የማስተላለፊያ መስመሮች ወይም የቴሌኮሙኒኬሽን መስመሮች መካከል በከፍተኛ ንፋስ ወቅት ሊኖር የሚገባው ርቀት፡ ኃይል በሚተላለፍባቸውና በማይተላለፍባቸው አካላት መካከል ሊኖር ከሚገባው ዝቅተኛ ርቀት በተጨማሪ ቢያንስ ፪.፭ ሜትር መሆን አለበት ።

፪· መስመሮቹ አንዱ ሌላውን በማቋረጥ የተዘረጉ ሲሆን ፡ ኃይል በሚተላለፍባቸውና በማይተላለፍባቸው አካላት መካከል ሊኖር ከሚገባው ዝቅተኛ ርቀት በተጨማሪ ፡ በከፍተኛ የአየር ሙቀት ወቅትና በአጎራባች ታወሮች ላይ የተወጠሩ ሽቦዎች በሚበጠሱበት አጋጣሚ መጠበቅ የሚገባው የከፍታ ርቀት ቢያንስ ፩.፭ ሜትር መሆን አለበት ።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተጠቀሱት መስመሮች የተለያየ ቮልቴጅ የሚኖራቸው ሲሆን ርቀቱ የሚወሰነው ከፍተኛውን ቮልቴጅ መሠረት በማድረግ ይሆናል ።

## ፷፩· ስለማከፋፈያ ጣቢያዎች

፩· የማንኛውም የማከፋፈያ ጣቢያ ዲዛይን የአቅርቦት አስተማማኝነትን ፡ የመስፋፋትና የመታደስ ብቃትንና ከአደጋ ሁኔታዎች መጠበቅን እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ አሠራርን ለማረጋገጥ በሚያስችል አኳኋን መከናወን አለበት ።

፪· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የማከፋፈያ ጣቢያ ቢያንስ አንድ የዝቅተኛ ቮልቴጅ መጋቢ መስመር እንዲኖረውና የወደፊቱን የኤሌክትሪክ ጭነት ዕድገት ምጣኔ መሠረት ያደረገና ቢያንስ የአምስት ዓመት የአቅርቦት ዋስትና የሚሰጥ ሆኖ ዲዛይን መደረግ አለበት ።

፫· የመሣሪያዎች መረጣ በብሔራዊ ደረጃዎች ወይም ብሔራዊ ደረጃዎች ከሌሉ በኢንተርናሽናል ኤሌክትሮ ቴክኒካል ኮሚሽን ደረጃዎች ላይ መመሥረትና ወቅታዊና የወደፊት ፍላጎቶችን እንዲሁም ኤጀንሲው በሥራ ላይ እንዲውል ያጸደቀውን የመሣሪያዎች አቀማመጥና ቅንጅት ያገናዘበ መሆን አለበት ።

## 59. *Clearance from Trees*

1) The vertical and horizontal distance of conductors from trees shall, at maximum temperature and with maximum wind, be at least 1.5 meters plus the minimum distance between live and unenergized parts.

2) In the case of fruit trees the distance referred to in Sub-Article (1) of this Article shall be 4 meters plus the minimum distance between live and unenergized parts.

3) The distances stated under Sub-Article (1) and (2) of this Article shall be maintained in accordance with the expected growth of trees.

## 60. *Clearance from Other Lines*

1) In the case of parallel lines the horizontal distance from the transmission line to the conductors of another transmission or telecommunication line shall, with maximum wind, be at least 2.5 meters plus the minimum distance between live and unenergized parts.

2) In the case of crossing lines the vertical distance between conductors shall, at maximum temperature and with conductors broken in the neighboring span, be 1.5 meters plus minimum distance between live and unenergized parts.

3) If the lines referred to in Sub-Article (2) of this Article have different voltage, the distance shall be determined according to the higher voltage.

## 61. *Substations*

1) Any substation design shall be carried out in such a way as to ensure supply security, extendability, maintainability capability of being extended, and safety as well as economical operations.

2) Without limiting the generality of Sub-Article (1) of this Article, any substation shall be designed with at least one low voltage feeder and a five year supply guarantee at the anticipated load growth rate.

3) The selection of equipment shall be based on the national standard or where such standard is not available on the International Electro-Technical Commission standards and shall consider both current and future system requirements and equipment layout standardization adopted by the Agency.

፬· የማከፋፈያ ጣቢያ የኤሌክትሪክ ዕቃዎች የማምረት ሥራ ሊጀመር የሚችለው የጣቢያው ንድፍ በኤጀንሲው ከጸደቀ በኋላ ብቻ ይሆናል፤ እንዲሁም በኤጀንሲው ያልጸደቀ ማንኛውንም ለውጥ በንድፉ ላይ ማድረግ አይቻልም ።

፭· የማከፋፈያ ጣቢያ የሚገነባበትን ቦታ በመምረጥ ረገድ የወጭ ቅነሳና እንደ መንገድ መኖር ፣ የመስፋፋት ችሎታ ፣ ለጭነት ማዕከላት ቅርበት ፣ ከብክለት ነጻ መሆንና የሠራተኞች ማኅበራዊና ባህላዊ ፍላጐቶችን ማሟላት የመሳሰሉ የጣቢያውን ሥራ ለማካሄድ የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች በቂ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል ።

ምዕራፍ ሦስት

ኤሌክትሪክ ስለማከፋፈል

፷፪· ስለማከፋፈያ መስመር ዲዛይን አጠቃላይ መስፈርቶች

፩· የማከፋፈያ ኔትወርክ ዲዛይን ፤
   ሀ) የወደፊቱን የመስፋፋት ዕቅድ ያገናዘበ ፤ እና
   ለ) በማከፋፈሉ ፈቃድ ዘመን ውስጥ ሊያጋጥሙ የሚችሉትን የአካባቢው የኤሌክትሪክ ጭነት ጠባዮችን ከግምት ውስጥ ያስገባ ፤

   መሆን አለበት ።

፪· የማከፋፈያ ኔትወርክ ዲዛይን የኤሌክትሪክ ብክነትን ፣ መቋረጥንና የሥራ ማስኬጃና የጥገና ወጪዎችን በመቀነስ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ሊያስገኝ በሚችል ሁኔታ መሠራት አለበት ።

፫· የማከፋፈያ ኔትወርክ አዘረጋግ ዲዛይን በአካባቢው ማስተር ፕላን ወይም ማስተር ፕላን ከሌለ በኤጀንሲው በጸደቀ ፕላን ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት።

፬· የማከፋፈያ ኔትወርክ ዕቃዎች መጠንና የግንባታ ዓይነት የብሔራዊ ደረጃዎችን ወይም ብሔራዊ ደረጃዎች ከሌሉ የኢንተርናሽናል ኤሌክትሮ ቴክኒካል ኮሚሽን ደረጃዎችን መስፈርቶች የተከተለ መሆን አለበት።

፷፫· ስለትራንስፎርመሮች

ለማከፋፈያ ኔትወርክ አገልግሎት የሚውሉ ትራንስፎርመሮች የአገልግሎትና የብቃት ደረጃ እንዲሁም የግንባታ ዓይነት በኤጀንሲው መመሪያ መሠረት ይወሰናል ።

፷፬· ስለምሰሶዎች አተካከል

፩· የኤሌክትሪክ ምሰሶዎች አተካከል ማስተር ፕላንን ወይም ማስተር ፕላን ከሌለ በኤጀንሲው የጸደቀ ፕላንን የተከተለ መሆን አለበት ።

፪· የኤሌክትሪክ ምሰሶዎች ርዝመትና በመካከላቸው የሚኖረው ርቀት የሚወሰነው በኤጀንሲው መመሪያ መሠረት ይሆናል ።

፷፭· የአገልግሎት መስመር

ማንኛውንም ወደ ደንበኞች የሚዘረጋ የኤሌክትሪክ መስመር ከምሰሶዎች ላይ ካልሆነ በስተቀር በመጥለፍ ማገናኘት አይቻልም ።

፷፮· የኤሌክትሪክ ኃይል ማከፋፈያና የመከላከያ ሽቦዎች

፩· የኤሌክትሪክ ኃይል ማከፋፈያና የመከላከያ ሽቦዎች በቴክኒካዊና ኢኮኖሚያዊ መስፈርቶች ተቀባይነት ያላቸው መሆን አለባቸው ።

፪· የሽቦዎቹ መጠን የሚመረጠው በብሔራዊ ደረጃዎች ወይም ብሔራዊ ደረጃዎች ከሌሉ በኢንተርናሽናል ኤሌክትሮ ቴክኒካል ኮሚሽን ደረጃዎች መሠረት ይሆናል ።

4) Production of electrical components shall be commenced only after the drawings have been approved by the Agency, and any subsequent change on the drawings shall not be made without the approval of the Agency.

5) Substation sites shall be selected with due regard to minimizing costs and satisfying functional requirements such as accessibility, expandability, proximity to load centers,avoidance of pollution and the social and cultural need of operators.

*CHAPTER THREE*

*Distribution*

62. *General Provisions for Distribution Line Design*

1) Distribution network design shall:
   (a) consider provision for future expansion; and
   (b) take into account the predicted load characteristics of the area for the duration of the distribution license.

2) Distribution network shall be designed to offer economic benefits by reducing electrical losses, black out and operational and maintenance costs.

3) The layout design of a distribution network shall be based on the master plan or where a master plan is not available on the plan approved by the Agency.

4) The size of the distribution network components and type of their structure shall be in conformity with the requirements of the national standard, or where such standard is not available, with that of the International Electro-Technical Commission standards.

63. *Transformers*

The functional and technical standards of transformers to be used in a distribution network and type of their structure shall be determined in accordance with directives of the Agency.

64. *Erection of Poles*

1) Erection of poles shall conform with master plans or where such master plans are not available with plans approved by the Agency.

2) The height and the span of electric poles shall be determined in accordance with directives of the Agency.

65. *Service Lines*

No service line or tapping shall be taken off an overhead line except at a point of support.

66. *Distribution System Conductors and Earth Wires*

1) Distribution system conductors and earth wires shall be technically and economically feasible.

2) The cross section of conductors and earth wires shall be selected in compliance with the national standard, or where such standard is not available, with the International Electro-Technical Commission standards.

፷፯. *መጠበቅ ስለሚገባቸው ርቀቶች*

የመካከለኛና ዝቅተኛ ቮልቴጅ ሽቦዎች ከሕንጻና ግንባታዎች ፣ ከአይሮፕላን መንደርደሪያ መንገዶች ፣ ከባቡር ሀዲዶች ፣ ከውሃ ላይ መንገዶች ፣ ከተለያዩ የመሬት አካላት ፣ ከኮሙኒኬሽን ሰርኪዩት ፣ በአየር ላይ ከተዘረጋ የማከፋፈያ ኬብልና ከመብረቅ መከላከያ ሽቦዎች የሚኖራቸው ርቀት እንዲሁም በፌዞች መካከልና ከመሬት በተገናኙና ኃይል፡ በሚተላለፍባቸው አካላት መካከል መጠበቅ የሚገባው ርቀት በኤጀንሲው መመሪያ መሠረት ይወሰናል ።

፷፰. *ስለኤሌክትሪክ ፍጆታ ቆጣሪዎች*

፩. የኤሌክትሪክ ፍጆታ ቆጣሪ ልዩ ልዩ ክፍሎች የአገልግሎትና የብቃት ደረጃ የብሔራዊ ደረጃዎችን ወይም ብሔራዊ ደረጃዎች ከሌሉ የኢንተርናሽናል ኤሌክትሮቴክኒካል ኮሚሽን ደረጃዎችን መስፈርት የሚያሟላ መሆን አለበት።

፪. የኤሌክትሪክ ፍጆታ ቆጣሪዎች ለደንበኞች ከመገጠማቸው በፊት በተገቢው የጭነት ደረጃ ካሊብሬት መደረግ አለባቸው ።

፷፱. *ኤሌክትሪክ ስለማከፋፈል አገልግሎት ጥራት*

፩. የኤሌክትሪክ ማከፋፈል አገልግሎት ጥራት የሚለካው በቀጣዮቹ አንቀጾችና በኤጀንሲው መመሪያ በተመለከተው አኳኋን የሚከተሉትን መስፈርቶች መሠረት በማድረግ ይሆናል ፤

ሀ) የቮልቴጅ ደረጃ ፤

ለ) የፌዞች መመጣጠን ፤

ሐ) ሁውከት የሚያስከትሉ ችግሮች ፣ ፈጣን የቮልቴጅ መርገብገብና ሀርሞኒክ ዲስቶርሽን አለመኖር ፤

መ) በኮሙኒኬሽን ሥርዓት ውስጥ ጣልቃ አለመግባት፡

ሠ) አማካይ የኃይል መቋረጥ ድግግሞሽ አነስተኛነት፡

ረ) አጠቃላይ የኃይል መቋረጥ የጊዜ መጠን አነስተኛነት ፤

ሰ) የፍጆታ ክፍያ አሰባሰብ ።

፪. ባለፈቃዱ የአገልግሎት ጥራትን ለመለካት የሚያስፈልጉ መረጃዎችን የመሰብሰብ ግዴታ ይኖርበታል ።

፸. *ስለቮልቴጅ ደረጃ*

ባለፈቃዱ የሚያሰራጨው የቮልቴጅ መጠን ከደንበኞች በሚያገናኙ ልዩ ልዩ መድረሻ ጫፎች ላይ እንደሚከተለው መሆን አለበት ፤

፩. የመካከለኛ ቮልቴጅ ፕራይመሪ ማከፋፈያ ሲሆን ፤

ሀ) መነሻው ፲፭ሺ ቮልት ሆኖ በ፲ ፐርሰንት ሊጨምር ወይም ሊቀንስ የሚችል ፤ እና

ለ) መነሻው ፴፫ሺ ቮልት ሆኖ በ፲ ፐርሰንት ሊጨምር ወይም ሊቀንስ የሚችል ፤

፪. የዝቅተኛ ቮልቴጅ ማከፋፈያ ሲሆን ፤

ሀ) መነሻው ፪፻፳ ቮልት ሆኖ በ፭ ፐርሰንት ሊጨምር ወይም ሊቀንስ የሚችል ፤ እና

ለ) መነሻው ፫፻፹ ቮልት ሆኖ በ፭ ፐርሰንት ሊጨምር ወይም ሊቀንስ የሚችል ።

፸፩. *ስለ ፍሪኩዌንሲና ፓወር ፋክተር*

፩. የሥርዓቱ ፍሪኩዌንሲ ፶ ኸርዝ ሆኖ በ፩ ፐርሰንት ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል ።

፪. የኤሌክትሪክን ኃይል ለንግድ ወይም ለኢንዱስትሪ የሚጠቀሙ ደንበኞች የሚገጥሟቸው ማሽኖችና መሣሪያዎች ፓወር ፋክተር ከዜሮ.፱ ማነስ የለበትም ።

67. *Clearances*

The distance from medium and low voltage conductors to buildings and structures, runways, rail roads, water ways, terrain, communication circuits, airial supply cables and lightning protection wires, and as well as clearance of conductors between phases and between earthed and live parts shall be determined in accordance with directives of the Agency.

68. *Electricity Consumption*

1) Components of electricity consumption meters shall meet all requirements regarding metering performance and efficiency set in the national standard or where such standard is not available in the International Electro-Technical Commission standards.

2) Electricity consumption meters shall be calibrated according to the appropriate load standards prior to their installations in customers' premises.

69. *Quality of Distribution Service*

1) Quality of distribution service shall be measured on the basis of the following parameters as determined by the subsequent Articles and directives of the Agency:

(a) voltage level;

(b) balance between phases;

(c) avoidance of disturbance, rapid voltage oscillation and harmonic distortion;

(d) non-interference in communication system;

(e) lower average interruption frequency;

(f) lower total interruption time; and

(g) billing service.

2) The licensee shall have the obligation to carry out gathering of information which is necessary to measure quality of service.

70. *Voltage Level*

The voltage supplied by the licensee at the receiving side in the various terminal of premises shall be:

1) in the case of primary distribution at medium voltage:

(a) 15000 volt plus or minus 10%; and

(b) 33000 volt plus or minus 10%;

2) in the case of distribution at low voltage;

(a) 220 volt plus or minus 5%; and

(b) 380 volt plus or minus 5%.

71. *Frequency and Power Factor*

1) The system frequency shall be 50 hertz plus or minus 1%.

2) The power factor of machinery and equipment installed by customers who use electricity for commercial or industrial purposes shall not be less than 0.9.

፸፪· የፌዞች መመጣጠን
፩· የኤሌክትሪክ ጭነቶች በባለፈቃዱ የሥርጭት ሥርዓት ውስጥ በየፌዞቹ መከፋፈል ይገባቸዋል።
፪· የአንድ ፌዝ ጭነት ከሌላ ፌዝ ጭነት ሲነጻጸር ከ፲ ፐርሰንት በላይ መብለጥ አይኖርበትም ።

፸፫· ስለዋጋ ማስከፈያ ኢንቮይሶች
፩· ባለፈቃዱ በፍጆታ ንባብ መሠረት ትክክለኛና ግልጽ የሆኑ የኤሌክትሪክ ፍጆታ ዋጋ ማስከፈያ ኢንቮይሶች ማቅረብ አለበት ።
፪· በኢንቮይሶች ላይ የሚከተሉት መረጃዎች ለደንበኞች መገለጽ አለባቸው ፤
ሀ) የመክፈያ ቦታ ፤
ለ) ደንበኞች የሚስተናገዱበት ቦታና ጊዜ ፤
ሐ) የአገልግሎት እጦት ቅሬታና የአደጋ ወይም የማንኛውም ሌላ ብልሽት ሪፖርት መቀበያ የስልክ ቁጥሮች ።

፸፬· የአቅርቦት አገልግሎትን ስለመቀጠል
ባለፈቃዱ በክፍያ መስተጓጎል ምክንያት አቋርጦት የነበረን የኤሌክትሪክ አቅርቦት አገልግሎት ደንበኛው የፍጆታንና የሚፈለግበትን ተጨማሪ ክፍያ በፈጸመ በ፳፬ ሰዓት ጊዜ ውስጥ መልሶ መቀጠል አለበት ።

፸፭· ስለደንበኞች ቅሬታ መዝገብ
፩· ባለፈቃዱ በሚሰጠው አገልግሎት አለመሟላት ወይም ከአገልግሎቱ ጋር በተያያዘ ማናቸውም ምክንያት በደንበኞች የሚቀርብለትን እያንዳንዱን ቅሬታ በመቀበል የቅሬታ አቅራቢውን የውል ቁጥርና ስም ፣ ቅሬታው የቀረበበትን ቀንና ሰዓት ከነምክንያቱ መመዝገብ አለበት።
፪· ባለፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(፩) መሠረት ለሚያደርግ የቅሬታ ምዝገባ የሚያገለግል የደንበኞች ቅሬታ መዝገብ በየንግድ አገልግሎት ጣቢያዎቹ ማኖር አለበት።

## ክፍል ስድስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፸፮· ስለሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት
፩· የኤሌክትሪክ ሥራ ተቋራጭነት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ለኤጀንሲው የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን መያዝ አለበት ፤
ሀ) የአመልካቹን ማንነትና አድራሻ ፤
ለ) አመልካቹ ያገኘው ዲግሪ፣ ዲፕሎማ ወይም የምስክር ወረቀት ካለው ይህንኑ ፤
ሐ) አመልካቹ የሥራ ልምድ ካለው ይህንኑ ፤
መ) ኤጀንሲው ያስፈልጋሉ ብሎ በመመሪያ የሚወስናቸውን ሌሎች መረጃዎች ።
፪· ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(፩) መሠረት የቀረቡለትን መረጃዎች ካጣራ በኋላ የአመልካቹን የሙያ ብቃትና ልምድ ለመገምገምና የምስክር ወረቀቱን ደረጃ ለመወሰን እንዳስፈላጊነቱ የጽሑፍና የተግባር ፈተና ሊሰጥ ይችላል ።
፫· ኤጀንሲው አመልካቹ የተወሰነውን ክፍያ ከከፈለ በኋላ በ፴ ቀናት ውስጥ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል።
፬· ለሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚጠየቀው ክፍያ እንደሚከተለው ይሆናል።

72. *Balance between Phases*
1) In facilities of the licensee the load must be distributed among the phases.
2) The ratio of the load in one phase shall not exceed by more than 10% of the load in any other phase.

73. *Invoicing*
1) The licensee shall issue clear and correct invoices for electricity consumption based on actual readings.
2) The following information shall be provided to customers on the invoice;
(a) the collection place;
(b) places and schedule of attention to customers;
(c) phone numbers to receive lack of service complaints and reports of accidents or any other irregularities.

74. *Supply Reinstatement*
In the case of disconnection on the ground of default in payment, the licensee shall reinstate the supply of electricity within 24 hours after the customer had effected payment for owed invoices plus the corresponding overcharges.

75. *Customer's Complaint Book*
1) Every customer's complaint for any deficiency in the service rendered or in any of its features shall be received and recorded by the licensee, taking note of the correlative number and customer's name, date and hour at which the complaint is received and its reason.
2) For the purpose of recording complaints under Sub-Article (1) of this Article, the licensee shall keep customers' complaints book at each of its commercial attention center.

## *PART SIX*
## *MISCELLANEOUS PROVISIONS*

76. *Certificate of Professional Competence*
1) Any application for the grant of certificate of professional competence for electrical contractors shall be addressed to the Agency and shall contain the following:
(a) identity and address of the applicant;
(b) degree, diploma or certificate acquired, if any;
(c) work experience, if any;
(d) any other information the Agency may determine by directives.
2) The Agency may, following verification of all information submitted in connection with the application under Sub-Article(1) of this Article, give a written and performance test, as may be appropriate, to evaluate the professional competence of the applicant and to determine the grade of the certificate.
3) The Agency shall, upon payment by the applicant of the prescribed fees, issue certificate of professional competence within 30 days.
4) Fees to be paid for the issuance of certificate of professional competence shall be as follows:

ሀ) ለደረጃ አንድ ................................ ብር ፭፻
ለ) ለደረጃ ሁለት ................................ ብር ፬፻
ሐ) ለደረጃ ሦስት ................................ ብር ፫፻
መ) እስከ ደረጃ አራት ለሚሆኑ ዝቅተኛ ደረጃዎች ................................ ብር ፩፻

፭· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ስለሚሰጥ ፈተናና ስለሙያ ብቃት የምስክር ወረቀት ደረጃዎች ሚኒስቴሩ ዝርዝር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

፸፯· <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

አግባብ ባላቸው የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች ለኤጀንሲው የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ለዚህ ደንብ አፈጻጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሚኒስቴሩ ሊያወጣ ይችላል።

፸፰· <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

፩· ይህ ደንብ ከመጽናቱ በፊት የኤሌክትሪክ ኃይል በማመንጨት፣ በማስተላለፍ ወይም በማከፋፈል ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ኤጀንሲው በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ በዚህ ደንብ መሠረት ፈቃድ ማውጣት አለበት።

፪· ይህ ደንብ ከመጽናቱ በፊት የኤሌክትሪክ ኃይል ለንግድ ላልሆነ አላማ በማመንጨት፣ በማስተላለፍ ወይም በማከፋፈል ተግባር ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ኤጀንሲው በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የአዋጁን አንቀጽ ፲ (፪) ድንጋጌ ማሟላት አለበት።

፫· ከአዋጁ መውጣት በፊት በቀድሞው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ መብራትና ኃይል ባለሥልጣን ተሰጥቶ የነበረ ማንኛውም የኤሌክትሪክ ተቋራጮች የሙያ ብቃት ምስክር ወረቀት ኤጀንሲው በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ በዚህ ደንብ መሠረት በሚሰጥ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እስከሚተካ ድረስ ጸንቶ ይቆያል።

፸፱· <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ግንቦት ፲፪ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር



(a) for grade one Birr 500
(b) for grade two Birr 400
(c) for grade three Birr 300
(d) for lower grades upto grade four Birr 100

5) The Ministry may issue detailed directives regarding examinations and grading of certificates of competence referred to under Sub-Article (2) of this Article.

77. *Power to Issue Directives*

Without prejudice to the powers given to the Agency under the appropriate provisions of these Regulations, the Ministry shall have the power to issue directives necessary for the proper implementation of these Regulations.

78. *Transitory Provisions*

1) Any person engaged in the operations of electric power generation, transmission or distribution business Prior to the coming into force of these regulations shall, within the period to be specified by the Agency, obtain a license to be issued in accordance with these Regulations.
2) Any person engaged in the operations of electric power generaton, transmission or distribution activity for non commercial purposes prior to the coming into force of these Regulations shall, within the period to be specified by the Agency, fulfill the requirements of Article 10(2) of the Proclamation.
3) Any electrical contractor's certificate of professional competence issued by the former Ethiopian Electric Light and Power Authority prior to the coming into force of the Proclamation shall remain valid until replaced by a certificate of professional competence issued pursuant to these Regulations within a period to be specified by the Agency.

79. *Effective Date*

These Regulations shall enter into force on the date of their publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa this 2o[th] day of May, 1999.

MELES ZENAWI
PRIME MINISTER
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

## ማረሚያ ቁጥር ፩/፲፱፻፺፩

ታህሣሥ ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም. በወጣው የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት (ማሻሻያ) ደንብ ላይ ከዚህ በታች ያለው ማረሚያ ተደርጓል፣

ሀ) "አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፯" የተባለው "አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፶፩" ተብሎ ይነበብ፣

ለ) "፱፻፵፪" እና "፱፻፵፫" የነበረው የገፆቹም ቁጥር በቅደም ተከተል "፩ሺ፳፭ እና ፩ሺ፳፮" ተብሎ ይነበብ ፡፡

## CORRIGENDUM No. 1/1999

The Customs Tariffs Council of Ministers (Amendment) Regulations of 25 December, 1998 is hereby corrected as follows:

a) the issue number "5th year No. 27" shall read "5th year No. 51"; and

b) the page numbers "942" and "943" shall read "1025" and "1026" respectively.

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE